# በግንባታ ውል ክርክር ላይ በተሰጡ ፍርዶች ላይ የቀረበ አስተያየት

ፋሲል ታደሰ*

ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነው ጉዳይ ሶስት የግንባታ ውሎችን እና እነዚህን ውሎች ለማሻሻል የተደረጉ የማሻሻያ ውሎችን ተከትሎ በስራ ተቋራጩ እና በአሠሪው መካከል የተነሱትን አለመግባባቶች በተመለከተ በመጀመሪያ በመሐንዲሱ የተሠጠ ውሳኔ እና ውሳኔው እንዲፈጸም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በነበረ የአፈፃፀም ክርክር ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በየደረጃው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርበው የተሰጡ ውሳኔዎች ናቸው::[1]

1. ስለጉዳዩ አጀማመርና የተሰጡ ውሳኔዎች

መግቢያ

1.1 አልመሽ ኃ.የተ.የግል ማህበር (አሰሪ) እና አሰፋ በለጠ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ (ስራ ተቋራጭ) በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአሳይታ ከተማ መስጊድ፣የመኖሪያ ቤቶችና ት/ቤት ለማሰራት ሰኔ 6 ቀን 1986ዓ.ም. እና ነሐሴ 26 ቀን 1986ዓ.ም. ሶስት የግንባታ ውሎችን የተዋዋሉ ሲሆን፤ባትኮዳ[2] የግንባታታውሎችን በተመለከተ ያወጣው "ደንብ" የውሎቹ አካል እንዲሆንም ተስማምተዋል:: በመቀጠልም ሶስቱንም ውሎች አሰመልክቶ ህዳር 19ቀን 1987ዓ.ም. የማሻሻያ ውሎች የተፈራረሙ ሲሆን በማሻሻያ ውሎቹ በባትኮዳ ከወጣው"ደንብ" ውስጥ በአንቀጽ 1(ሐ እና መ) እና አንቀጽ 67 የተደነገጉትን አሻሽለዋል::[3] በነዚሁ ማሻሻያ ውሎች ወስጥ አቶ

---

* (ኤል.ኤል.ቢ - ሕግ ፋክልቲ -አ.አ.ዩ.) የሕግ አማካሪና ጠበቃ

[1] እነዚህኑ ውሳኔዎች መነሻ በማድረግ በግንባታ ውሎች ውስጥ የሚነሱ አንዳንድ ጉዳዮችንም እግረመንገዳችንን አጭር ምልከታእእናደርግባቸዋለን::

[2] ይህ ቃል በእንግሊዝኛ ሙሉ አጠራሩ "Building and Transport Construction Design Authority"(BaTCoDA)በአማርኛ ደግሞ "የህንፃና ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን ባለስልጣን" ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 327/1979ዓ.ም. የተቋቋመውን የባለስልጣን መ/ቤት ለመግለጽ በውሎቹም ሆነ በፍ/ቤቶቹ ውሳኔዎች ውስጥ የሚገኝ ነው:: በዚህ ጽሁፍ ውስጥም ይህንኑ ስያሜ ለመጠቀም እንገደዳለን:: ባትኮዳ ከተቋቋመበት ዓላማዎች አንዱ የግንባታ ስራዎች ውል አካል ሊሆኑ የሚገባቸውን ጠቅላላ የውል ሁኔታዎችን (General Conditions of Contract)የሚዘረዝሩ ሰነዶችን ማውጣት ነው:: በዚሁም መሠረት በእንግሊዝኛው አጠራሩ "Standard Conditions of Contract for the Construction of Civil works Projects, 1987" በመባል የሚታወቀውን ስታንዳርድ በማውጣት በስራ ላይ እእንዲውል አድርጓል:: ይህ ሰነድ ወደ 75 አንቀጾችን፣የግንባታ ውል ፎርምን (Form of Agreement)እእና የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ፎርም (Performance Bond)በአባሪነት ይዟል::ታ

[3] በባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1ሐ "መሐንዲስ" ማለት "የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ሆኖ በባትኮዳ በፅሁፍ መሐንዲስ ተብሎ የተሰየመ ሲሆን ፤በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ባትኮዳ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቷል:: በሌላ በኩል የደንቡ አንቀጽ 67 በስራ ተቋራጭና በአሰሪ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በቅድሚያ ውሳኔ የሚሰጠው መሐንዲሱ መሆኑን፣መሐንዲሱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘው ወገን በውሳኔው ላይ ውሳኔው በደረሰው በ90 ቀን ውስጥ

ወንድወሰን አበበ የተባሉ መሐንዲስ በተዋዋዮቹ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን አስመልክቶ ውሳኔእንዲሰጡ ተስማምተዋል:: በዚሁ መሠረት ግንባታው እየተከናወነ ባለበት ወቅት በክፍያ ምስክር ወረቀት ቁ.5 ጥቅምት ወር 1989ዓ.ም. ላይ መሐንዲሱ ለስራ ተቋራጩ ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ መጠን አረጋግጦ ለአሰሪው ላከ:: ሆኖም ይህ ሳይፈጸም እጅግ እየዘገየ የስራ ተቋራጩም አቤቱታ እየበረታ የፕሮጀክቱም አፈጻጸም እየተጓተተ ሄዶ በሰኔ ወር 1991ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. ጁን 30ቀን 1999)ፕሮጀክቱ ታገደ:: በመቀጠልም ስራ ተቋራጩ ግንባታውን ለሚድሮክ ኮንስትራክሽንእንዲያስረክብ ተደረገ:: ይህንንም ተከትሎ ስራተቋራጩ ይገባኛል የሚለውን ክፍያ እንዲፈጸምለት የተለያዩ ጥረቶችን ማድረጉን ገልጾ በመጨረሻም ሐምሌ 13 ቀን 1996ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. ጁላይ 12 ቀን 2004)በተፃፈ ደብዳቤ ሰራኋቸው ለሚላቸው ግንባታዎችና አሰሪው ግዴታውን ባለመወጣቱ ሊከፈለኝ ይገባል ያለውን ገንዘብ እንዲከፈለው እንዲወስንለት ለመሐንዲሱ ለአቶ ወንድወሰን አበበ አቤቱታ አቀረበ:: መሐንዲሱም መስከረም 6 ቀን 1997 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. ሴፕተምበር 16 ቀን 2004) አሰሪው ለስራ ተቋራጩ በጠቅላላው ብር 19,760,954.79(አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከ79/100) እንዲከፍለው ውሳኔ ሰጡ::

## 1.2 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር እና የተሰጠው ውሣኔ

ስራ ተቋራጩ የመሐንዲሱ ውሳኔ እንዲፈፀምላቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት (ፌ/ከ/ፍ/ቤት) በመ.ቁ 37147 የአፈፃፀም ፋይል ከፈቱ:: በመዝገቡ የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ የቀረበው አሰሪው መጋቢት 7 ቀን 1998ዓ.ም. በሰጠው መልስ የባትኮዳን ደንቦች ከራሱ ከባትኮዳ በቀር ተዋዋይ ወገኖች ሊያሻሽሉት እንደማይችሉ፣መሐንዲሱ በባለዕዳው የተቀጠሩት የማሻሻያ ውሎቹ ተፈረሙ ከተባለበት ቀን ሁለት ዓመት የሚጠጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ መሆኑን፣ስለዚህም አማካሪ መሐንዲስ ሆነው ሊሰየሙ እንደማይችሉ፣ ከባለዕዳው ጋር የነበራቸው ውል ጥር 4 ቀን 1996ዓ.ም. የተቋረጠ በመሆኑ ከባለመብቱ ተመራላቸው የተባለውን አለመግባባት አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልነበራቸው መሆኑን፣መሐንዲሱ በመሐንዲስነት ተሹመዋል ቢባል እንኳ ባትኮዳ ባወጣቸው ደንብ አንቀጽ 1(ሸ)መሠረት የባትኮዳን የፅሁፍ ስምምነት (ልዩ ፈቃድ)ሳያገኙ ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ሊሰጡ አይችሉም:: እንዲሁም መሐንዲሱ በስነስርዓት ሕጉ ሊከተሉ

---

ለባትኮዳ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል፣የባትኮዳ ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ መሆኑንና ሌሎችንም ጉዳዮች ይደነግጋል::

በውሳኔዎቹ የተጠቀሱት ተከራካሪዎች በደንቡ ላይ ባደረጉት ማሻሻያ መሐንዲሱን እራሳቸው የመረጡት መሆኑን ስለባትኮዳ የተሰጠውን ትርጉም ቀሪ ያደረጉት መሆኑንና አለመግባባት ስለሚፈታበት ሁኔታ የተደነገገውን አንቀጽ 67 በተመለከተ ደግሞ የተመደበው መሐንዲስ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለባትኮዳ ሳይሆን ለሽምግልና ጉባኤ(Arbitration)እ እንዲያቀርብ ተስማምተዋል::

የሚገባቸውን የሙግት ስርዓት ሳይከተሉ ውሳኔ ሰጥተዋል የሚሉ ክርክሮችን በማቅረብ የመሐንዲሱ ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል አይደለም በማለት ተከራክሯል:: በግራቀኙ በፅሁፍ ከቀረቡት ክርክሮች በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ግንቦት 1 ቀን 1998ዓ.ም. ግራቀኝ ወገኖችን በቃል እንዳከራከረ መዝግቧል::

በመጨረሻም ጥቅምት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የውሳኔው ፍሬ ሃሳብ የሚከተለው ነበር::

- አቶ ወንድወሰን አበበ የኮንስትራክሽኑን ስራ እንዲቆጣጠሩ በባለዕዳው የተቀጠሩት የማሻሻያ ውሎቹ ከተፈረሙ በኋላ ስለመሆኑ ባለዕዳው ያቀረበው ማስረጃ ቢያረጋግጥም በማሻሻያ ውሎቹ እኚሁ ሰው ስለመመደባቸው ስለተረጋገጠ፣እንዲሁም መሐንዲሱ ውሳኔያቸውን ከሰጡበት ቀን በጣም ቀደም ብሎ በመሐንዲሱና በባለዕደው መካከል የነበረው ውል የተቋረጠ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም ባለዕዳው ይህንኑ ሁኔታ ለባለመብቱ በፅሁፍ አላሳወቀም፤ሌላ መሐንዲስም ስላልተካ የባለዕዳው ክርክር ተቀባይነት የለውም::
- መሐንዲሱ የሙግት ስርዓቱን ተከትሎ የበኩሌን ክርክር እንዳቀርብ ዕድል አልሰጠኝም የሚለውን የባለዕዳውን ክርክር በተመለከተ ደግሞ ባለዕዳው ይህ ጥፋት ተፈፅሞብኛል የሚል ከሆነ በወቅቱ በመሐንዲሱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ በማሻሻያው በተቀመጠው ስርዓትና የጊዜ ገደብ ይግባኝ ማቅረብ ነበረበት እንጂ አሁን ይህን መከራከሪያ ሊያቀርብ አይገባም::
- የባትኮዳ "ደንብ" አንቀጽ 2(1)(ሸ) ግራቀኙ በተፈራረምዋቸው የማሻሻያ ውሎች "በግልጽ አለመሰረዙ ወይም አለመሻሻሉ አላከራከረም::"ሆኖም ባለመብቱና ባለዕዳው ባደረጓቸው ማሻሻያ ውሎች የባትኮዳን አንቀጽ 67ን በማሻሻል በደንቡ ባትኮዳ የነበረውን የይግባኝ ሰሚነትን ስልጣን ቀሪ ያደረጉ በመሆኑ፣ መሐንዲሱ ጉዳዮችን አይቶ ለመወሰን የባትኮዳን ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልገው የመሐንዲሱን ውሳኔ በይግባኝ የሚመለከተው ባትኮዳ ቢሆን ነበር፣"የደንቡ አንቀጽ 67 ድንጋጌ በማሻሻያ ውሎቹ በሌላ ድንጋጌ መተካት ግራቀኙ የአንቀጽ 2(1)(ሸ)ድንጋጌ በመካከላቸው በሚኖር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን በአንድምታ መስማማታቸውን የሚያመለክት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ያምናል::" ግራቀኝ ተዋዋይ ወገኖች የባትኮዳን ደንብ በስምምነት እንደተቀበሉ ሁሉ በስምምነት የማሻሻል ነፃነት አላቸው::"በዚህም ሁኔታ መሐንዲሱ ውሳኔውን ለመስጠት የባትኮዳን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ ነበረበት በማለት ከባለዕዳው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ ፍ/ቤቱ አላገኘውም::"በማለት የመሐንዲሱን ውሳኔ የፍርድ ባለዕዳው እንዲፈፅም ወስኗል:: በዚሁ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘው ባለዕዳው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.27478 ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የካቲት 25 ቀን 2000ዓ.ም. በዋለው ችሎት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔን አፅንቷል::

## 1.3 በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክርና የተሰጠው ውሳኔ

ባለዕዳው ክፍብለን በተራቁ. 1.2 በገለፅናቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘቱ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.36577 አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም "መሐንዲሱ ሰጠ የተባለው ውሳኔ ግራቀኙ ካደረጉትና ከባትኮዳ አኳያ በፍርድ ሊፈጸም የሚችል መሆን፣ አለመሆኑን፣እንዲሁም ፈቃድ የማግኘትን ሁኔታ በስምምነት ያስቀሩት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር" ያስቀርባል በማለት ባለመብቱ በተጠሪነት ቀርቦ እንዲከራከር በማድረግ የግራቀኙን የጽሁፍ እና የቃል ክርክሮች አዳምጧል:: ግራቀኙ ወገኖች በሰበር ችሎቱ ያቀረቧቸው ክርክሮች በስር ፍ/ቤቶች አቅርበዋቸው ከነበሩት ክርክሮች የተለዩ ባለመሆናቸው በድጋሚ በዚህ ክፍል ማስፈሩ አስፈላጊ አይደለም::

የሰበር ችሎቱ በአመልካቹና በተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር ለመወሰን "ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል ነው አይደለም የሚለውን ለመመለስ በቅድሚያ ውሳኔውን ሰጡ የተባሉት መሐንዲስ ውሳኔውን ለመስጠት ሥልጣን ነበራቸው ወይ የሚለውን ነጥብ መመርመር ያስበት" መሆኑን ገልጾ ከዚህ ጭብጥ አንፃር የራሱን ትንተና በመስጠት በፌ/ከ/ፍ/ቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የሻረ ሲሆን የውሳኔው ፍሬ ሃሳብ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ነበር::

- በግራቀኙ በተደረጉት "...የማሻሻያ ውሎች ከባትኮዳ ደንቦች የተሻሻሉት መሐንዲሱን ባትኮዳ ከሚሰይመው ይልቅ አሰሪው የሚሰይመው መሆኑን፣የባትኮዳ ትርጉም ለግራቀኙ ግንኙነት ተፈፃሚ እንደማይሆን፣ እንዲሁም የክርክር መፍቻ ዘዴን ስርዓት በሚመለከት ብቻ ነው:: ከነዚህ ደንቦች በቀር ሌላ ማሻሻያ ስላልተደረገ ቀሪዎቹ የባትኮዳ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል:: ስለዚህም አለመግባባቱን ለመወሰን በአሰሪው የተሰየሙት መሐንዲስ አለመግባባቱን መዳኘት ከመጀመራቸው በፊት በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት የባትኮዳን ልዩ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል::..."
- "የደንቡ አንቀጽ 2 መሐንዲሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሌሎች የተዘረዘሩ ጉዳዮች ለመዳኘት ከባትኮዳ ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልገው መሆኑን በአስገዳጅነት አስቀምጧል::" ያለ ሲሆን አያይዞም ይህ ሁኔታ ያስፈለገበትን ምክንያቶች ናቸው ያለውን የራሱን አስተያየት ሰጥቷል::
- በማጠቃለያውም ተዋዋዮቹ "... መሐንዲሱ አለመግባባቱን አይቶ ለመወሰን ከባትኮዳ ሊያገኝ የሚገባውን ልዩ ፈቃድ የማግኘት ቅድመ ሁኔታን ያላሻሻሉ በመሆኑና መሐንዲሱ ይህንን ፈቃድ ስለማግኘቱ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ስለሌለ መሐንዲሱ ውሳኔውን ለመስጠት በሕግ ስልጣን አይኖረውም::... ስለዚህም የስር ፍ/ቤት ከባትኮዳ ልዩ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሐንዲስ

የሠጡት ውሳኔ እንዲፈፀም ትዕዛዝ መስጠቱ እና ይግባኝሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል::"

## 2. ስለግንባታ ውሎች አጭር ምልከታ

ከግንባታ ጋር በተያያዘ በሀገራችን ባሉ ሕጎች ውስጥ በተለያዩ አዋጆች እና አዋጆቹን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ለግንባታ ውል ትርጉም ተሰጥቷል::[4] ከእነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች መረዳት የሚቻለው የግንባታ ውሎች ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገኛኙ መሆናቸውን ነው::

የግንባታ ውል የሚደረገው በአሰሪው (ባለቤት፣ኢንቨስተር በሚባሉ ስሞችም ይታወቃል)እና በስራ ተቋራጩ መካከል ነው:: በሌላ በኩል ከአሰሪው ጋር በሚገባው የሙያ አገልግሎት ውል (የአሰሪው ተቀጣሪ ሠራተኛ ሊሆንም ይችላል) የግንባታውን ስራ የሚቆጣጠር፣ለተሰራው ስራ ለስራ ተቋራጩ ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የሚያረጋግጥ፣በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በውሉ ሊሰሩ ስምምነት የተደረሰባቸውን ስራዎች እንዳስፈላጊነቱ የመለዋወጥ፣የስራዎቹን መጠን የመጨመር እና የመቀነስ ትዕዛዝ የመስጠት፣እንደሁኔታው በአሰሪው እና በስራ ተቋራጩ መካከል ከውሉ አፈፃፀም ጋር የሚነሱ አለመግባባቶችን ተመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ የሚሰጥ አማካሪ መሐንዲስ[5] (ተቆጣጣሪ መሐንዲስ፣ፕሮጀክት ማናጀር...በሌሎችም ስያሜ ይታወቃል )አለ::

አማካሪ መሐንዲስ (በሕንፃ አዋጅ ቁ.624/2001ዓ.ም.የተመዘገበ ባለሙያ በመባልም ይጠራል)በግንባታ ውል ውስጥ ሁለት ዓይነት ሚና አለው::የመጀመሪያውና በግልፅ የሚታየው ከአሰሪው ጋር በገባው የሙያ አገልግሎት ውል መሠረት ግንባታው በውሉ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን

---

[4] በባትኮዳ ማቋቋሚያ አዋጅቁ.327/1979 አንቀጽ 2(1)"የሕንፃ ኮንስትራክሽን" ማለት ማናቸውም በከፊል ወይም በሙሉ የወለል፣የግድግዳና የጣሪያ ስራ ያለው ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚውል ሕንፃና ተዛማጅ ስራዎች የመስራት ወይም የማሻሻል ስራ ነው"በማለት ትርጉም የተሰጠ ሲሆን፣በአንቀጽ2(2) ደግሞ "የትራንስፖርት ክንስትራክሽን" ማለት የመንገዶች፣የድልድዮች፣የባቡር ሃዲዶች፣የአይሮፕላን ማረፊያዎች የወደቦችና የየብስ ማመላለሻ ተርሚናሎች የመስራት ወይም የማሻሻል ሥራ" እንደሆነ ተደንግጓል::

- "ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ስራ ውል" በሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 3019(1)የስራ ተቋራጭነት ውል"የሕንፃን ስራ ለመስራት የተሰራውን ለማደስ ወይም አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማደራጀት ..." እንደሚደረግ ይደነግጋል::
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የመንግስት የግዥ ስርዓትን ለመወሰንና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁ. 430/1997 በአንቀጽ 2(ሐ) ስር "የግንባታ ዘርፍ ስራ" ማለት ከሕንፃ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ ልማት ስራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣የማፍረስ፣የጥገና፣የማደስ ስራ እንዲሁም ተጓዳኝ አገልግሎት..." እንደሆነ ይደነግጋል::

[5]የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.691/2003 ዓ.ም. አንቀጽ 25(1)(ቸ)እንደተደነገገው የስራና ከተማልማት ሚንስቴር በዚህ ሙያ ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ማህበራት የሙያ ችሎታታ ማረጋገጫ የመስጠት ደረጃዎችን የመወሰን፣የመመዝገብ እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል::

መቆጣጠር ሲሆን በዚህኛው ገፅ ሙሉ በሙሉ የአሰሪው ወኪል ነው::[6] ከአሠሪው በተሰጠው ውክልና መሠረት ወኪሉ የአሠሪውን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ተግባሩን ይፈፅማል:: በሌላ በኩል ደግሞ በአሠሪው እና በስራ ተቋራጩ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ላይ ውሳኔ ይሠጣል:: ይኸኛው ተግባሩ ብዙ ክርክሮችን ያስነሳል:: የወኪሉን ጥቅም የማስጠበቅና የማስቀደም ኃላፊነት በሕግ የተጣለበት አማካሪ መሐንዲስ ወካዩ በሆነው አሠሪ እና ስራ ተቋራጭ መካከል የሚነሳውን አለመግባባት በገለልተኝነት እና በነፃነት አይቶ ሊወስን ይችላልን? የሚለው በቀዳሚነት የሚነሳ ጥያቄ ነው::

ከፍብለንእእንደገለጽነው በግንባታ ውል አፈፃፀም ሂደት ውስጥ አሰሪ፣ስራ ተቋራጭና አማካሪ መሐንዲስ በመባል የሚታወቁ ወገኖች ያሉ ሲሆን በአሠሪውና በስራ ተቋራጩ እንዲሁም በአሠሪውና በአማካሪ መሐንዲሱ መካከል በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት አለ:: ነገር ግን በስራ ተቋራጩና በአማካሪ መሐንዲሱ መካከል ምንም ዓይነት የውል ግንኙነት የለም:: ሆኖም የግንባታው ውል ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ እስከማብቂያው ድረስ በሁለቱ ወገኖች መካከል በጣም የጠበቀ የስራ ግንኙነት አለ:: በዚህ ግንኙነት ውስጥ አማካሪ መሐንዲሱ አሠሪውን በመወከል ስራ ተቋራጩ እንደውሉ ግንባታውን እያከናወነ መሆኑን ይቆጣጠራል:: ይህን ተግባሩን ለማከናወን የተለያዩ ትዕዛዞችን ለስራ ተቋራጩ ያስተላልፋል:: ስራ ተቋራጩም ትዕዛዙን ከውሉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት::

በዚህ ግንኙነት ውስጥ የሚነሳው ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ከአሠሪው የተሰጠው የውክልና ስልጣን ጉዳይ ነው:: በውለታው ሰነዶች ውስጥ አማካሪ መሐንዲሱ በራሡ በቀጥታ የሚያከናውናቸው ተግባሮች ያሉ ሲሆን አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ ደግሞ የአሠሪውን ፈቃድ በማግኘት ብቻ የሚያከናውናቸው ይሆናሉ:: በዚህ ሂደት (ግን ኙነት) ውስጥ አማካሪ መሐንዲሱ በሥራ ተቋራጩ ላይ ጉዳት ቢያደርስ ስራተቋራጩ መብቱን

---

[6] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የግዥ ስርዓትን ለመወሰንና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁ.430/1997 ዓ.ም. የተቋቋመው ባለስልጣን በአንቀጽ 11 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በ1998 ዓ.ም. ካወጣው የግዥ ሰነድ የውሎች ጠቅላላ ሁኔታ (General Conditions of Contract) አንቀጽ 4 ላይ "በዚሁ ሰነድ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ እና የተቀመጡት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው መሐንዲሱ በአሠሪው እና ስራ ተቋራጩ መካከል ውለታውን በተመለከተ በሚነሱ ጉዳዮች አሰሪውን በመወከል ይወስናል::" ( "Except where otherwise specifically stated and subject to any restriction in the special condition of Contract, the Engineer will decide contractual matters between the Employer and the Contractor <u>in the role representing the Employer.</u>" (ሥርዝ የተጨመረ)

- ይህ አማካሪው መሐንዲስ የሚገኝበት ሁኔታ በጣም ግልፅ የሚሆነው መሐንዲሱ የአሠሪው ተቀጣሪ ሠራተኛ በሚሆንበት ጊዜ ነው::ይህ በእኛ ሃገርም ሆነ በሌሎች ሀገሮች የሚታይ ጉዳይ ነው:: በሀገራችን አንዳንድ የመንግስት ተቋማት በመዋቅራቸው ውስጥ የተለያየ ስያሜ በመስጠት ይህን የአማካሪነት ስራ የሚሰራ ክፍል እና ባለሙያዎች ይኖራቸዋል:: ለምሳሌ ያህል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን መጥቀስ ይቻላል::

ለማስከበር የሚያቀርበው ጥያቄ በምን ላይ የተመሠረተ ይሆናል የሚለው ነው:: በመካከላቸው የውል ግንኙነት ባለመኖሩ በውል ላይ ተመስርቶ ስራ ተቋራጩ ሊጠይቀው የሚችለው ጉዳይ አይኖርም:: ስለዚህ ከውል ውጭ ኃላፊነት ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በሕጉ የተደነገገውን አማራጭ መጠቀም ግድ ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜም ከአሠሪው ጋር በጣምራ ኃላፊ የሚሆኑበት አጋጣሚም ይኖራል::

የግንባታ ውል ከመፈረሙ በፊትም ሆነ በኋላ ከፍተኛ የሆኑ በሰነዶች ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶች ያለበት ነው:: ለምሣሌ ያህል የግንባታ ውሉ ከመፈረሙ በፊት በአሰሪና በምሕንድስና ባለሙያዎች መካከል በሚኖር ውል የአርክቴክቸራል፣ የስትራክቸራል፣የኤሌክትሪካል፣የሳኒቴሪ እና ሌሎች የተለያዩ ዲዛይኖች ይከናወናሉ:: እነዚህ ሁሉ ስራዎች በስዕል (Drawing, plans...) እና በፅሁፍ ዝርዝር (Specification) ይገለፃሉ:: ወደ ማጠቃለያውም መጠናቸውን እና አይነታቸውን የሚዘረዝር (Bill of Quantities)ሰነድ ይዘጋጃል:: ይህ ብቻም አይደለም:: እንደሁኔታው በመንግስታዊ[7] ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ሙያነክ ማህበራት[8] የሚዘጋጁ ጠቅላላ የውል ሁኔታዎችን የሚደነግጉ (General Conditions of Contract/Standard Conditions of Contract) )ሰነዶች በቀጥታ በማስገባት ወይም በመጥቀስ የውሉ አካል እንዲሆኑ ይደረጋል:: ተዋዋይ ወገኖች እነዚህን ጠቅላላ የውል ሁኔታዎችን ለራሳቸው ውል በሚፈልጉት መንገድ በማሻሻል ልዩ የውል ሁኔታዎችን (Particular Applications of Contract" በመባል ይታወቃሉ)ይደነግጋሉ:: የግንባታ ውል የሚፈረመው ከፍብለን የዘረዘርናቸው ተግባራት ከተፈጸሙ በኋላ ነው::

3. **በፍርዶቹ ላይ የተሰጠ አስተያየት**

---

[7] በግርጌ ማስታወሻ ተራ ቁ.6 የተገፈውን ይመልከቱ:: እንደሁም በዚህ ፅሁፍ መግቢያ ላይ በተጠቀሱት የመሐንዲሱ እና የፍ/ቤቶቹ ውሣኔዎች ተደጋግሞ የሚጠቀሰውን ባትኮዳ አውጥቶት የነበረውን እና እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 1994 የስራና ከተማ ልማት ሚንስቴር በተቋቋመበት አዋጅ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ያወጣውን የውል ሁኔታዎችን መጥቀስ ይቻላል:: ስለአስተዳደር መ/ቤት ውሎች የሚደነግገው የፍ/ብሔር ሕጉ ከአንቀጽ 3135-3139 እንደዚህ ዓይነት ጠቅላላ የውል ሁኔታዎችን እያንዳንዱ አስተዳደር መ/ቤት እንደሚያዘጋጃቸው ገልፆ የሕግ ውጤታቸውንም ዘርዝሯል::

[8] በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀባይነት ያላቸውን ለግንባታ ውሎች የሚውሉ የውል ጠቅላላ ሁኔታዎችንና እነዚሁ ጠቅላላ ሁኔታዎች ወደ ልዩ የውል ሁኔታዎች ማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያዎችን (Legal Guide to prepare Particular Conditions)በማዘጋጀት የሚታወቀው የዓለም አቀፍ የአማካሪ መሐንዲሶች ፌዴሬሽን (Federation Internationale DesIngenieurs-Conseils-FIDIC ተብሎ በአህፅሮተ ቃል የሚታወቀው)እና የተለያዩ ሀገራት ብሔራዊ የአማካሪ መሐንዲሶች ማህበር በጋራ ያቋቋሙት ማህበር ነው:: ይህ ማህበር ዋናው ጽ/ቤቱን ስዊዘርላንድ ላውሳን በምትባል ከተማ አድርጎ እ.ኤ.አ. ከ1913 ጀምሮ ያለ ማህበር ነው::

እ.ኤ.አ. በ1987 ባትኮዳ አውጥቶት የነበረው የውል ጠቅላላ ሁኔታም ሆነ በዲሴምበር 1994 በስራና ከተማ ልማት ሚንስቴር የወጣው የውል ጠቅላላ ሁኔታ የፊዲክ ቅጅዎች ናቸው::

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል የምናያቸው ነጥቦች፤

1. በየደረጃው ባሉት ፍርድቤቶች በተከራካሪ ወገኖች ተነስተው ውሳኔ ያረፈባቸው እና ውሳኔ ያላረፈባቸው ነጥቦችን በተመለከተ እና
2. በተከራካሪዎቹ ያልተነሡ ፍርድቤቶቹም ያልተመለከቷቸውና ቢመለከቷቸው ኖሮ በሚል ሊነሡ የሚችሉ ነጥቦች የሚሉ ናቸው፡፡

### 3.1 <u>በየደረጃው ባሉት ፍርድቤቶች በተከራካሪ ወገኖች ተነስተው ውሳኔ ያረፈባቸው እና ውሳኔ ያላረፈባቸው ነጥቦችን በተመለከተ</u>

ክርክሮቹን በአጭሩ ለማስታወስ ያክል ለፍርዶቹ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪው እና ስራ ተቋራጩ መካከል የነበረውን የግንባታ ውል ይቆጣጠሩ የነበሩት መሐንዲስ አሠሪው ለስራ ተቋራጩ ብር 19,760,954.79(አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከ79/100) እንዲከፍል የሠጡት ውሳኔ እንዲፈጸምለት ስራ ተቋራጩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአፈፃፀም ክስ መመስረቱ ሲሆን ለቀረበበት የአፈፃፀም ክስ አሰሪው የሠጠው መልስ 1ኛ/ የባትኮዳን ደንብ ተዋዋይ ወገኖች ማሻሻል አይችሉም 2ኛ/ መሐንዲሱ የማሻሻያ ውሎቹ በተፈረመበት ጊዜ በአሠሪው ያልተቀጠሩ በመሆኑ በመሐንዲስነት ሊሰየሙ አይችሉም፣ስራተቋራጩ ይገባኛል የሚሉትን ጥያቄ ለመሐንዲሱ ካቀረበበት ወቅት ቀደም ብሎ በአሠሪውና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ከተሰናበቱ በኋላ ተመራላቸው የተባለውን አለመግባባት አይተው የመወሰን ስልጣን አልነበራቸውም 3ኛ/ መሐንዲሱ ከባትኮዳ በፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ የሠጡት ውሳኔ አስገዳጅነት ሊኖረው አይገባም እና 4ኛ/ መሐንዲሱ ውሳኔ የሰጡት በሙግት ስርዓት የተደነገጉትን አክብረው አሠሪውን ሳይጠሩና ሳያከራክሩ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሠሪው የቀረቡትን መከራከሪያዎች አንድ በአንድ በመመርመር የራሱን ምክንያት በመስጠት በሙሉ ውድቅ አደርጓቸዋል፡፡ በዚህ ፍርድ ቅር የተሰኘው አሰሪው ስርዓቱን ጠብቆ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክርክር ሲሆን ስራ ተቋራጩ በበኩሉ በመካከላቸው በተደረጉት ማሻሻያ ውሎች የባትኮዳን “ደንብ” አሻሽለው በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት መሐንዲሱ አይተው እንዲወስኑ መስማማታቸውን ፣በዚሁ መሠረት መሐንዲሱ ውሳኔ መስጠታቸውን፣ውሳኔ መስጠቱን አሠሪው በጊዜው ያወቁት ቢሆንም ይግባኝ ስላላቀረቡ ውሳኔው የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ነው በማለት መልስ ስጥቷል፡፡

ጉዳዩን በመጨረሻ ያየው የሰበር ችሎቱ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሊፈፀም የሚችል ነው አይደለም የሚለውን ለመወሰን

"በቅድሚያ ውሳኔውን ሰጡ የተባሉት መሐንዲስ ውሳኔውን ለመስጠት ስልጣን ነበራቸው ወይ" የሚል ጭብጥ በመያዝ ባትኮዳ ባወጣው ደንብ አንቀጽ 2(1) /ሸ/ ላይ መሐንዲሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የባትኮዳን የፅሁፍ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት የሚል በመሆኑና ይህንንም ድንጋጌ ተዋዋዮቹ ያላሻሻሉት በመሆኑ፣ መሐንዲሱ የባትኮዳን ፈቃድ ሳያገኝ የሠጠው ውሳኔ አስገዳጅ አይደለም በማለት ወስኗል::

የዚህ ፅሁፍ ፀሀፊ የሰበር ችሎቱ ከያዘው ጭብጥም ሆነ በጭብጡ ላይ በሰጠው ውሳኔ ይስማማል:: ሆኖም በዚህ ጭብጥ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ችሎቱ ከሰጠው ምክንያት የሚቀድም ሌላ ወሳኝ ነጥብ አለ:: ይህም በአሠሪውና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው የውል ግንኙነት መቋረጥ /ያለመቋረጡ ጉዳይ ነው:: አሠሪው መሐንዲሱን የቀጠርኩት ሕዳር 19 ቀን 1987 ዓ.ም. ከስራ ተቋራጩ ጋር ያደረግናቸውን የማሻሻያ ውሎች ካደረግን ከሁለት ዓመት በኋላ ነው በማለት የሚያቀርበውን ክርክር ለጊዜው ትተነው ስራተቋራጩ ለመሐንዲሱ አቤቱታውን ካቀረበበት ሐምሌ 5 ቀን 1996 ዓ.ም. ሆነ መሐንዲሱ ውሳኔ ከሠጠበት መስከረም 6 ቀን 1997 ዓ.ም. ቀደም ብሎ ጥር 4 ቀን 1996 ዓ.ም. ላይ በአሠሪውና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው ውል ተቋርጧል:: እነዚህ ፍሬነገሮች በሚገባ የተረጋገጡ ናቸው::

እነዚህን በመደገፍ አሠሪው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገው የውሉ መቋረጥ በአሠሪውና በመሐንዲሱ መካከል ብቻ ውጤት ከሚያመጣ በቀር በስራ ተቋራጩ ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም የሚል ምክንያት ሰጥቶ ነው:: በሌላ በኩል የሰበር ሰሚችሎቱ በዚህ ነጥብ ላይ ምንም ያለው ነገር የለም:: መሐንዲሱ በአሠሪው የተሰየመ ነው:: በግንባታ ውሎች እንደሚታወቀው አማካሪ (ተቆጣጣሪ) መሐንዲስ የአሠሪው ወኪል ነው:: አሠሪውን በመወከል ስራውን ይቆጣጠራል:: በአሰሪውና በመሐንዲሱ መካከል የሙያ አገልግሎት ውል ወይም የቅጥር ውል አለ:: አሠሪው መሐንዲሱን በሙሉ ፈቃዱ መርጦ እንደቀጠረው ሁሉ በራሱ ፀሳኔ ውሉን ሊያቋርጠው ይችላል:: አማካሪ መሐንዲስ የግንባታ ስራውን ተቆጣጥሮ የማሠራት እና በአሰሪውና በስራ ተቋራጩ መካከል የሚነሱትን አለመግባባቶች የመወሰን ስልጣኑ ምንጭ ከአሠሪው ጋር ያለው ውል ነው:: ስራተቋራጩ አሰሪው የመደበውን አማካሪ መሐንዲስ ከመቀበል ውጭ (ውሉን ከማቋረጥ በቀር ማለቴ ነው) ሌላ ምንም ምርጫ የለውም:: አማካሪ መሐንዲስ በስራተቋራጩ እና በአሠሪው መካከል አለመግባባቶችን አይቶ ውሳኔ ይሰጣል መባሉ በግራቀኙ መካከል በጋራ ስምምነት የተመረጠ "ዳኛ" አያደርገውም:: ይህንንም ስራተቋራጩ ተስማምቶ የተቀበለው የውል ግዴታው ነው::

በአማካሪ መሐንዲሱ፣በአሠሪው እና በስራተቋራጩ መካከል በሕግና በውል ያለው ግንኙነት ከፍብለን እንደገለጽነው ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሠሪው እና በመሐንዲሱ መካከል ያለው ውል መቋቋሙም ሆነ መቋረጡ ሁለቱን ወገኖች ከሚመለከት በቀር

በስራተራቋጩ ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ አይችልም በማለት የሰጠው ፍርድ ትክክል አይደለም። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ፍ/ቤቱ አሰሪው ከመሐንዲሱ ጋር የነበረውን የስራ ውል አቋርጫለሁ ካለ በኋላ ተተኪ መሐንዲስ የሰየመ መሆኑን ለስራተቋራጩ በጽሁፍ አለማሳወቁን ለፍርዱ እንደማጠናከሪያ በማድረግ የሰጠው ምክንያትም ቢሆን ከፍብለን ከገለጽናቸው ምክንያቶች አንፃር ትክክል አይደለም።

ከፍብለን እንደገለጽነው በአሰሪውና በመሐንዲሱ መካከል ያለው ውል መቋረጡ ስለሚያስከትለው ውጤት የሰበር ችሎቱ በውሳኔው ምንም ያለው ነገር የለም። የሰበር ችሎቱ መሐንዲሱ ውሳኔ ለመስጠት የባትኮዳን ልዩ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋቸው ነበር፤ይህን ሳያገኙ የሰጡት ውሳኔ ሊፈጸም አይችልም ብሎ ወስኗል። የሰበር ችሎቱን ውሳኔ በተቃራኒው ብንመለከተው (a contrario reasoning) መሐንዲሱ የባትኮዳን ፈቃድ በፅሁፍ ካገኙ በኋላ ውሳኔ ሰጥተው ቢሆን ኖሮ የሰበር ችሎቱ የመሐንዲሱ ውሳኔ ሊፈፀም የሚችል ነው ብሎ ይወስን ነበር ማለት ይቻላል። ይህ አባባል የሰበርችሎቱ በአሰሪው እና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው ውል መቋረጡ ስለሚያስከትለው ውጤት ሊኖረው የሚችለውን አቋም ግን የሚገልጽ አይሆንም።

እንደዚህ ፀሀፊ እምነት የሰበር ችሎቱ ለጉዳዩ እልባት ከሰጠበት ነጥብ ይልቅ በአሰሪው እና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው ውል የመቋረጡን ውጤት ቀድሞ ሊያየው እና ሊወስንበት የሚገባ ነበር። በአሰሪው እና በመሐንዲሱ መካከል የነበረው ውል ከተቋረጠበት ጊዜ አንስቶ መሐንዲሱ በአሰሪውና በስራተቋራጩ መካከል በነበረው የግንባታ ውል ውስጥ የነበራቸው የመሐንዲስነት ተግባር ሙሉ በሙሉ ቀሪ ሆኗል። በእርግጥ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም እንደሚስማማው የመሐንዲሱ ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል አይደለም። ሆኖም የሰበር ችሎቱ ውል የመቋረጡን ውጤት ቀድሞ ቢያየው ኖሮ ምንም ስልጣን ሳይኖር በተሰጠ ውሳኔ እና ከስልጣኑ በላይ ወይም ደግሞ ተግባሩን ለመፈፀም የሚያስፈልገው ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ በተሰጠ (በሚሰጥ) ውሳኔ መካከል ያለውን የጎላ ልዩነት እና ትርጉም ለማሳየት ይችል ነበር። ምናልባትም ችሎቱ የወሰነውን ጭብጥ ማየትም ላያስፈልገው ይችል ነበር።

**"ተዋዋይ ወገኖች የባትኮዳን ደንብ ማሻሻል ይችላሉ አይችሉም የሚለው ክርክር" በተመለከተ**

ይህ ነጥብ በሁሉም ፍ/ቤቶች ተነስቶ የነበረ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የስር ፍ/ቤት አቋም ተዋዋይ ወገኖች በፈቃዳቸው የባትኮዳን "ደንብ" የውላቸው አካል እንዲሆን እንደተስማሙ ሁሉ የደንቡን የተለያዩ ድንጋጌዎች በስምምነት የማሻሻል ነፃነት አላቸው የሚል ሲሆን ሰበር ችሎቱ ግን በዚህ ነጥብ ላይ ምንም ሳይል ይልቁኑም አንጠልጥሎት ነው ያለፈው። በዚህ ነጥብ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የያዘው አቋም ትክክል ነው። የባትኮዳን "ደንብ" እራሱ ባትኮዳ ካልሆነ በቀር ተዋዋይ ወገኖች ሊያሻሽሉት አይችሉም የሚለውን ክርክር ያቀረበው

አሰሪው ነው። እንደዚህ አይነት ክርክሮች እና በተመሳሳይ ሁኔታ ባትኮዳም ሆነ ስራና ከተማ ልማት ሚንስቴር ያወጣቸው የውል ጠቅላላ ሁኔታዎች በቀጥታ እንደ ሕግ ተፈፃሚ ናቸው የሚሉ ክርክሮች ይነሣሉ። ለክርክሮቹ መሠረት የሆነው ምን ሊሆን ይችላል ብሎ ለሚጠይቅ ሰው በመጀመሪያ የሚታሰበው መልስ እነዚህ ሰነዶች "ደንብ"እእየተባሉ መጠራታቸው ያመጣው ችግር አንድ መልስ ነው።

በዚህ ነጥብ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የያዘው አቋም በፍ/ብ/ሕጉ "ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች" (General Conditions)በመንግስታዊ ተቋማት ሊወጡ እንደሚችሉ፤ የወጡ የውል ጠቅላላ ሁኔታዎች ውጤት (Effects) ከተደነገገው ጋር የሚስማማ ነው። በፍ/ሕግ ቁ.3138(1) እንደተደነገገው እንደዚህ ዓይነት ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች በእያንዳንዱ ውል ላይ በግልጽ ተመልክተው ካልተጠቀሱ በቀር በቀጥታ ተፈፃሚ አይሆኑም። በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁ. (2) ደግሞ በአንድ ውል ላይ በተለይ የተዘረዘሩ የውል ሁኔታዎች በጠቅላላ በውሎች ሁኔታ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሊሽሩ እንደሚችሉ ተደንግጓል። የመንግስት የግዥ ሰነዶችን የማዘጋጀትና መፈጸማቸውን የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ግዢ ኤጀንሲ ለግንባታ ውሎች የሚውሉ ሰነዶች በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚከተለው ስርዓት ጠቅላላ የውል ሁኔታዎችን (General Conditions of Contract)እና እነዚህን የሚያሻሽሉ ልዩ የውል ሁኔታዎችን (Special Conditions of Contract) በሚፈቅድ መልኩ ነው። ከዚህም አልፎ የኤጀንሲውን የፅሁፍ ስምምነት በቅድሚያ በማግኘት "ከተፈቀደ መደበኛ የግዥ ሰነዶች አሰራሩን ከሚመሩ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጪ ግዥ"ሊፈጸም እንደሚችል በሕጉ ተደንግጓል።[9]

3.2

<u>ተከራካሪዎቹ ያልተነሡ ፍርድቤቶቹም ያልተመለከቷቸውና ቢመለከቷቸው ኖሮ በሚል ሊነሡ የሚችሉ ነጥቦች</u>

ዋናዎቹ ውሎች በአሰሪና በስራተቋራጩ መካከል በመጀመሪያ ጊዜ የተፈረሙት ሰኔ 6 ቀን 1986 እና ነሐሴ 20 ቀን 1986 ዓ.ም. ሲሆን፤የማሻሻያ ውሎቹን የተፈራረሙት ደግሞ ሕዳር 19 ቀን 1987 ዓ.ም. ነበር። ባትኮዳ የተባለው መንግስታዊ ተቋም ያወጣው የግንባታ ውሎች ጠቅላላ ሁኔታ (በተከራካሪዎቹም ሆነ በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔዎች ውስጥ ደንብ እየተባለ የሚጠቀሰው)የመጀመሪያዎቹ ውሎች አካል እንዲሆን ግራቀኙ የተስማሙ ሲሆን፤በማሻሻያዎቹ ውሎች ውስጥ በስምምነት ካሻሻሏቸው የባትኮዳ ድንጋጌዎች በቀር የባትኮዳ ሰነድ የውለታዎቹ አካል መሆኑ ቀጥሎ ባለበት ጊዜም ሆነ

[9] አዋጅ ቁ.430/1997 ዓ.ም. አንቀጽ 11(4እና5)እና አንቀጽ 35 ይመለከቷል።

በፍ/ቤቶቹ ክርክር በሚደረግበት ወቅት ይኸው ባትኮዳ (በሙሉ ስሙ "የሕንፃና የትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን ባለስልጣን" በእንግሊዝኛ አጠራሩ ደግሞ "The Building and Transport Construction Design Authority" በመባል የሚታወቀው) የተባለው ተቋም የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 327/1979ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 41/1985 ዓ.ም.[10] ተሽሮ የባትኮዳ መብቶችና ግዴታዎች በዚሁ አዋጅ ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

ሆኖም ምንም ማስረጃ ሳይቀርብበት የተረጋገጠው እና መረጋገጡም የዳኝነት ግምት (Judicial Notice)ሊወስድበት የሚገባው የባትኮዳ ሕልውና ማብቃት ጉዳይ በተከራካሪዎቹም አልተነሳም፡፡ ፍርድቤቶቹም አልተመለከቱትም፡፡[11] በሌላ በኩል ተከራካሪዎቹ ወገኖች ዋናዎቹን ውሎችም ሆነ ማሻሻያዎቹን ሲፈራረሙ ባትኮዳ የተቋቋመበት አዋጅ መሻሩም ሆነ ስልጣንና ተግባሩ ወደ ሌላ ሚኒስቴር መ/ቤት የተላለፈ መሆኑን አያውቁም ነበር ብሎ በእርግጠኝነት መፃፍ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስህተቶች ከፍተኛ በሆኑ ሰነዶች በሚቋቋመው የግንባታ ውሎች ውስጥ የሚያጋጥሙ ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቀደም ብለው የተዘጋጁና የተፈረሙ ውሎችን የተዋዋይ ወገኖችን ስም፣አድራሻቸውን፣ሊሠራ የታሰበውን ስራዎች ዝርዝር እና ዋጋ ብቻ በመለወጥ (Copy & Paste በማድረግ)ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የሚዘጋጁ ውሎች ለከፍተኛ አለመግባባት እና ጉዳት ይዳርጋሉ፡፡[12]

ከፍብለን ያነሳነውን የባትኮዳን በሕግ ሕልውናው የማብቃቱን ነገር በመከራከሪያነት ቢያነሳው የሚጠቀመው ወገን አቀረበው ወይም ደግሞ የሰበርሰሚው ችሎት የሕግ ጥያቄን ያስከትላል ብሎ አነሳው

---

[10] ይሄው አዋጅ ቁ.41/1985 (እንደተሻሻለ)በአዋጅቁ.4/1987 ዓ.ም. የተሻረ ሲሆን ይህም አዋጅ እራሱ በአዋጅ ቁጥሮች 93/1990፣134/1991፣256/1994፣380/1996፣411/1996 እና 465/1997 የተሻሻለ ቢሆንም በአዋጅ ቁ. 471/1998 ተሽሯል፡፡ ይኸው አዋጅ ቁ. 471/1998 ዓ.ም. (እንደተሻሻለ) በአዋጅ ቁ.691/2003ዓ.ም. የተሻረ ሲሆን ይኸው አዋጅ ደግሞ በማረሚያ ቁ.7/2003 የታረመ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥሮች 720/2004 እና 723/2004 ተሻሽሏል፡፡

[11] በእርግጥ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ካለበት ገደብ አንፃር በግራ ቀኙ ያልተነሱ ጉዳዮችን በራሱ አልተመለከተም ተብሎ ትችት ማቅረቡ አግባብ ላይሆን ይችላል፡፡

[12] የዚህ ጽሁፍ ጸሀፊ በፍ/ቤትና የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካሎች ዘንድ በሚታዩ የግንባታ ውሎችን በሚመለከቱ ክርክሮች ላይ እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ገጥሚቸዋል፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ተዋዋዮቹ ወገኖች የውላቸው አካል እንዲሆኑ በሚዘረዝሩበት ክፍል ውስጥ ሕልውናው ያበቃው ባትኮዳ ያወጣው ጠቅላላ ሁኔታ እና የስራ ከተማ ልማት ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 1994 ያወጣው የውሎች ጠቅላላ ሁኔታ በአንድ ላይ የውለታው አካል ናቸው ብለው ተስማምተውባቸዋል፡፡ በአንድ ሌላ ጉዳይ ደግሞ በተዋዋዮቹ መካከል የውለታው ጠቅላላ ሁኔታዎች እንዲሆን የተጠቀሰው የመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በ1998 ዓ.ም. ያወጣው ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች ሆኖ ነገር ግን የዚህ ውል አካል በሆነ እና የውሎችን መሠረታዊ ነጥቦችን በአጭሩ በሚያስቀምጠው አባሪ ውስጥ ደግሞ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አውጥቶት የነበረው የውል ሁኔታዎች አንቀጾች ተጠቅሰዋል፡፡

የሚል ግምት (assumption) በመያዝ ምን ውጤቶች ሊከተሉ ይችሉ ነበር የሚሉ እና ተያያዥ ጉዳዮችን አንስተን እንወያይ፡፡
በቅድሚያ ግን ፅሁፌን የምቀጥለው የተወሰኑ ነጥቦችን ግልፅ በማድረግ ይሆናል፡፡ ከፍብዬ በተራቁ. 3.1 በመሐንዲሱ እና በአሠሪው መካከል የነበረው ውል ቀደም ብሎ የተቋረጠ በመሆኑ መሐንዲሱ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምንም ዓይነት ስልጣን የለውም በማለት የገለፅኩት አቋሜን አልለወጥኩም፡፡ ስለዚህም በፅሁፌ ለመቀጠል መሐንዲሱ ጉዳዮን ተመልክተው በወሰኑባቸው ጊዜያቶች በሙሉ ከአሠሪው ጋር የነበራቸው የውል ግንኙነት አልተቋረጠም ማለት ግድ ይሆናል፡፡

**ሀ. <u>ሕልውናው በአዋጅ ያበቃለት ባትኮዳ በተዋዋዮቹ ወገኖች መጠቀሱ እና በፍ/ቤቶቹም መደገሙ</u>**

ከፍብለን በተደጋጋሚ እንደገለፅነው ተዋዋዮቹ ወገኖች የመጀመሪያዎቹ ውሎቻቸውን ከተፈራረሙበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ ቀደም ብሎ ባትኮዳን ያቋቋመው አዋጅ ቁ.327/1979ዓ.ም. በአዋጅ ቁ.41/1985ዓ.ም. ተሽሯል፡፡ ተከራካሪዎቹም ሆኑ ፍ/ቤቶቹ በሌለ ተቋም ላይ በመደገፍ (የሌለ ተቋምን በመጥቀስ)ያቀረቧቸው ክርክሮች እና የሠጧቸው ፍርዶች ምንም ትርጉም የላቸውም፡፡

**ለ. <u>የባትኮዳ "መብቶች እና ግዴታዎች" በአዋጅ ቁ. 41/1985ዓ.ም. አንቀጽ 60(2) የተላለፉለት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴርስ?</u>**

በርዕሱ በተጠቀሰው አዋጅ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፉት የባትኮዳ መብቶች እና ግዴታዎች ናቸው፡፡ በአሰሪው የተነሳው ክርክር እና በሰበርሰሚው ችሎትም አስፈላጊ እና አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ነው ተብሎ የተጠቀሰው የጽሁፍ ፈቃድ ለመሐንዲሱ የመስጠት ጉዳይ የባትኮዳ "መብቶች እና ግዴታዎች" ውስጥ ሊካተት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በማለት ሊነሳ የሚችል ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ውሎቹ በተፈጸሙበት ጊዜ ባትኮዳ "በህይወት" ባለመኖሩ ሊቀበለው የሚችለው ነገር የለም፡፡ ስለዚህም ሊያስተላልፈው የሚችለው ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን ባትኮዳ በአዋጅ ከመፍረሱ በፊት ባትኮዳን በማስገባት በተደረጉ የግንባታ ውሎች የተጀመሩ እና ሳይጠናቀቁ ባትኮዳ በአዋጅ መፍረሱ ለዚህ ጽሁፍ መነሻ በሆኑት ፍርዶች ላይ ከተጠቀሱት ውሎች የሚለይ በመሆኑ በተለየ ሁኔታ ሊታይ ይገባል ማለት ይቻል ይሆናል፡፡[13] ይሄም ሁኔታ ቢሆን አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን ያስነሳል፡፡ የተወሰኑ የጥቦችን እንመልከት፡፡

---

[13] ከዚህ ጋር በተያያዘ ብሔራዊ መሐንዲሶችና ስራተቋራጭ ድርጅት (ብ.መ.ስ.ተ.ድ/ስራ ተቋራጭ)እና ዘፍኮ ኃ.የተ.የግ.ማ(ዘፍኮ/አሠሪው)መካከል የነበረው ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ አሠሪው እና ስራ ተቋራጩ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለስድስት ፎቅ ሕንፃ የመገንባት ውል መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም. ተዋውለው የነበረ ሲሆን በውቀቱ ባትኮዳ የነበረ ሲሆን በባትኮዳ ዕውቀት ኤኪፕ ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማሕበር (ኤኪፕ)አማካሪ መሐንዲስ ሆኖ በአሠሪው ተሰይሟል፡፡ በሌላ በኩል አሠሪው እና ስራተቋራጩ ሐምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም. የማሻሻያ ውል ሲያደርጉ ባትኮዳ አልነበረም፡፡ ምናልባትም ከዚህ ቀን በፊት ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በውሉ አፈፃፀም ላይ መግባት ጀምሯል፡፡ በአሠሪው እና በስራ ተቋራጩ መካከል የነበረውን ውል አፈፃፀም ይቆጣጠር እና ያስተዳድር የነበረው

በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 13 ላይ በዘረዘርነው ጉዳይ ላይ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ለአፈፃፀም እስከሄደበት ጊዜ ድረስ ሁለቱም ወገኖች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ አልነበረም:: በመካከላቸው የነበረው ውል የአስተዳደር መ/ቤት ነው? የሚለው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ ግራቀኙ ወገኖች በፈ ፀሟቸው ተግባራቶች (አሠሪውም የአማካሪ መሐንዲሱን ውሳኔ ለማሻር ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አቤቱታ በማቅረቡ ስራተቋራጩም ለዚሁ አቤቱታ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት መልስ በመስጠቱ) የሚኒስቴር መ/ቤቱን የመዳኘት ስልጣን ተቀብለዋል ማለት ይቻላል::

ነገር ግን በስልጣኑ ላይ ተቃውሞ ለማስነሳት የሚያስችሉ መከራከሪያዎች ነበሩ ብሎ ይህ ፀሀፊ ያምናል:: አንዱ ነጥብ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፈለት የባትኮዳ "መብቶች እና ግዴታዎች" በመካከላችን ያለውን ጉዳይ መዳኘትን አያካትትም የሚለው ነው:: ባትኮዳን ያቋቋመው መንግስት ይከተለው ከነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር ከመንግስት ውጭ ያለው ሕብረተሰብ በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረው ተሣትፎ ውስን ነበር:: በሁሉም ጉዳይ ውስጥ መንግስት የገባበት እና የተቆጣጠረው በመሆኑ የባትኮዳ ተሣትፎ ሠፊ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም:: ሆኖም ከ1983 ዓ.ም. የመንግስት ለውጥ በኋላ አዲሱ መንግስት ከሚከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር የተቃኙት ሕጎች አካል የሆነው አዋጅ ቁ. 41/1985 ዓ.ም. እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጡት ሕጎች የሚኒስቴሩ ስልጣን በሀገሪቱ የግንባታ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጠቅላላ ፖሊሲና ስታንዳርዶችን ከማውጣት ጋር የተያያዘ ሆኖ ጉልህ ተሣትፎው በመንግስት ባጀት ከሚሠሩ ግንባታዎች ጋር የተያያዘ ነው:: ስለዚህም በግለሰቦች መካከል በሚነሱ የግንባታ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የመዳኘት ስልጣን አለኝ ብሎ ሊገባ አይችልም የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ ይችላል::

በሌላ በኩል ሊነሣ የሚችለው የተዋዋዮቹ ውል የማድረግ ነፃነት ነው:: ለምሳሌ ያህል በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የወጣው የግንባታ ውሎች ጠቅላላ ሁኔታ (Standard Conditions of Contract for Construction of Civil Work Projects, December 1994)ተዋዋይ ወገኖች የውላቸው አካል እንዲሆን ካልተስማሙ በቀር ሕግ ሆኖ በቀጥታ ሊፈፀም የሚችል

---

ኤኪፕ የሕንፃውን ጊዜያዊ ርክክብ ተከትሎ አሰሪው ለስራተቋራጩ ክፍያ እንዲፈጽም በሰጠው "ውሳኔ" ላይ አሠሪው ቅሬታ አለኝ በማለት ወደስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሄዷል:: ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሚያዚያ 29 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ የስራተቋራጩ የክፍያ ጥያቄ አግባብ ነው በማለት ወስኗል::

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ እንዲፈፀምለት የስራተቋራጩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ፍ/ብ/ቀ/ክስ ችሎት በመ/ቁ.11720 (የቀድሞው መ/ቁ.91/92) የአፈፃፀም ክስ ከፍቶ የነበረ ቢሆንም አሠሪው በመካከላችን ያለው ውል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ስለሆነ እና የአስተዳደር መ/ቤት ውል ደግሞ ለሽምግልና ዳኝነት አይቀርብም የሚል ክርክር በማቅረቡ ፍ/ቤቱም የአሠሪውን ክርክር በመቀበል የተሰጠው ውሳኔ ከመነሻውም ሕገወጥ ነው ሊፈፀም አይችልም በማለት ጥቅምት 9 ቀን 1996 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል:: በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው ስራተቋራጩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝሰሚው ፍ/ቤትም በመ/ቁ.13678 ታህሳስ 26 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤትን ትዕዛዝ አፅንቶታል::

አይደለም። ባትኮዳን ባቋቋመው አዋጅ ውስጥ በባትኮዳ የሚወጡ የውል ጠቅላላ ሁኔታዎችን የሕግ ውጤት አስመልክቶ በግልፅ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም። በግልፅም ሆነ በትርጉም ሊደርስበት በሚችል አገላለፅ የግንባታ ውሎችን አስመልክቶ ለባትኮዳ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣንም የለም። ይህን ስልጣን ባትኮዳም ሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያገኙት ተቋማቱ ያወጧቸውን ሰነዶች ተዋዋይ ወገኖች የውሎቻቸው አካል ሲያደርጓቸው ብቻ ነው። ስለዚህ ባትኮዳ በህይወት በነበረበት ጊዜ ባትኮዳን ታሳቢ በማድረግ የተዋዋሉ እና ለባትኮዳ የዳኝነት ስልጣን ሠጥተውት የነበሩት ወገኖች ባትኮዳ ሕልውናው ሲያበቃ በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት በሁለተኛ ደረጃ የሚያይና የሚወስን ተቋም (ግለሰብ)የመምረጥ መብታቸው ሊከበር ስለሚገባ በቀጥታ ሚኒስቴሩ ባትኮዳን በመተካት "ዳኛ" ሆኖ ሊገባ አይችልም በማለት ክርክር ሊቀርብ ይችላል።

**ማጠቃለያ**

4.1 ለዚህ ፅሁፍ መነሻ በሆኑት ፍርዶች እንደተመለከተው ሶስት ወገኖች በግንባታ ውል ውስጥ አሉ። እነርሱም አሠሪው፣ስራተቋራጩ እና አማካሪ (ተቆጣጣሪው)መሐንዲስ ሲሆኑ በአሠሪው እና በስራተቋራጩ መካከል የውል ግንኙነት አለ። በሌላ በኩል በአሠሪው እና በአማካሪ መሐንዲሱ መካከል የሙያ አገልግሎት ውል ወይም የቀጣሪ እና የተቀጣሪ ውል አለ። በስራተቋራጩ እና በአማካሪው መሐንዲስ መካከል ግን ምንም የውል ግንኙነት የለም።

4.2 በስራተቋራጩና በአማካሪ መሐንዲሱ መካከል የውል ግንኙነት የሌለ ቢሆንም መሐንዲሱ ከአሠሪው ጋር ባለው የውል ግንኙነት መነሻ አሠሪውን በመወከል ስራተቋራጩ ከአሠሪው ጋር በገባው ውል መሠረት ግንባታውን እያከናወነ መሆኑን፣ለተሠራው ስራ ሊከፈለው የሚገባውን መጠን የማረጋገጥ፣የለውጥ ስራ ትዕዛዝ መስጠት፣...ሌላው ቀርቶ በአሠሪውና በስራተቋራጩ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ተመልክቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው። አማካሪ መሐንዲሱ ሁለት ኃላፊነት አለበት፤የአሠሪው ወኪል ነው። የዳኝነት ሚናም አለው። የነዚህ ሁለት ኃላፊነት ምንጩ ከአሠሪው ጋር የገባው ውል ነው። አማካሪ መሐንዲሱ በተዋዋዮቹ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን አይቶ በመጀመሪያ ደረጃ የመወሰን ሥልጣን አለው መባሉ መሐንዲሱ የአሠሪው ወኪልና ተቀጣሪ መሆኑን ሊያስዘነጋም አይገባም።

ከፍብለን ያየናቸው ሁለት ፍርዶች ከዚህ አንፃር ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው። የከፍተኛው ፍ/ቤት በመሐንዲሱና በአሠሪው መካከል ያለው ውል ቀደም ብሎ የተቋረጠ ለመሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ክርክር ቢቀርብለትም ክርክሩን ውድቅ ያደረገበት ምክንያት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ካለማጤን የመጣ ነው። በሌላ በኩል የሰበርሰሚው ችሎት ይህን በቅድሚያ ሊያየው የሚገባውን ነጥብ ሳያይ መሐንዲሱ የባትኮዳን የፅሁፍ ፈቃድ በቅድሚያ ሳያገኝ የሠጠው ፍርድ ሊፈፀም የሚችል አይደለም ወደሚለው ነጥብመሄድአልነበረበትም።

## መመስከሪያ ማመሳከሪያ

ይህ የፕሮጀክት መሐንዲሱ ውሳኔ እንዲፈጸምላቸው የሥራ ተቋራጩ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.37147 የአፈጻጸም ፋይል የከፈቱ ሲሆን ተከሳሹም ቀርቦ ውሳኔው ሊፈጸም አይገባም በማለት ስለተቃወመ ፍ/ቤቱ ጥቅምት 14 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት በጉዳዩ ላይ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቶአል::

•ዳኛ:-ሙስጠፋ አህመድ::

የፍርድ ባለመብት በ02-06-98 ዓ.ም. በተጻፈና ፍ/ቤቱ በ25-05-98 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተሻሽሎ በቀረበ የአፈጻጸም ማመልከቻ፤

1. የፍ/ባለመብቱና የፍ/ባለዕዳው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአሳይታ ከተማ የሚሠሩ ሶስት (ማለትም የመስጊድ፣የመኖሪያ ቤቶችና የትምህርት ቤት) የግንባታ ሥራዎችን አስመልክቶ ሰኔ 6 ቀን 1986 ዓ.ም. እእና ነሐሴ 26 ቀን 1986 ዓ.ም. ውል ያደረጉ መሆኑን፣ የእነዚሁ ሶስት ውሎች አካል ነው የተባለውን «The Standard Conditions of Contract for the Construction of Civil Works Project BATCODA, December 1987» አንቀጽ 1(C)፣1(D) እና አንቀጽ 67 ድንጋጌዎችን ለማሻሻል ሁለቱም ወገኖችእ.ኤ.አ. በ28-11-94 (ኅዳር 19 ቀን 1987 ዓ.ም) ለሶስቱም ውሎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ሰስት የማሻሻያ ውሎች የተፈራረሙ መሆኑን፣

2. በማሻሻያ ውሎቹ መሰረት በሁለቱ ወገኖች መካከል በዋናዎቹ የግንባታ ውሎች አፈጻጸም ላይ ልዩነት ከተፈጠረ መሐንዲሱ አቶ ወንድወሰን አበበ ጉዳዩን ተመልክተው ውሳኔ እንዲሰጡ ስምምነት የተደረገ መሆኑን፣በዚህ መዝገብ አፈጻጸም የተጠየቀውንም ውሳኔ መሐንዲሱ እ.ኤ.አ. በ16-09-2004 (መስከረም 6 ቀን 1997 ዓ.ም.) በውሎቹ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የሰጡ መሆኑን፣በማሻሻያ ውሎች አንቀጽ 2(1)(B) መሰረት መሐንዲሱ በሰጡት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ውሳኔው በደረሰው በ45 ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለሌላኛው ወገን በጽሑፍ መግለጽ የነበረበት ቢሆንም ውሳኔው በ08-02-97 ዓ.ም. የደረሰው ባለዕዳው ይህ የአፈጻጸም አቤቱታእእስከቀረበበት ቀን ድረስ በውሳኔው ቅሬታ ያለው ስለመሆኑ የገለጸው ነገር ስለሌለ በውሉ መሠረት ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑን፣

3. መሐንዲሱ ከላይ በተገለጸው መሠረት የፍ/ባለዕዳው ለፍ/ባለመብቱ በአጠቃላይ ብር 19,760,954.79 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) እንዲከፍል ውሳኔ የሰጡ መሆኑን፣ባለዕዳው በውሳኔው ቅሬታ ያለው መሆኑን እስካልገለጸ ድረስ ውሳኔው በ30 ቀናት ውስጥ መፈጸም ሲገባው እስከአሁን ድረስ ያልፈጸመ መሆኑን፣

በመዘርዘር ባለዕዳው ይህንኑ በመሐንዲሱ የተወሰነውን ገንዘብ በማሻሻያ ውሎቹ መሠረት መክፈል ከነበረበት ከኅዳር 8 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ ወለድ ጋር ለባለመብቱ እንዲከፍል፣ በአፈጻጸም አቤቱታው ምክንያት የወጣውን የዳኝነት፣የቴምብር ቀረጥና የጠበቃ አበል ለባለመብቱ እእንዲተካ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ፣በማለት የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 316፣319 እና 378 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የጠየቀ ሲሆን በ02-06-98 ዓ.ም. ከተፈጸመ ማስረጃ መግለጫ ጋርም ዋናዎቹንና የማሻሻያ ውሎቹን፣የመሐንዲሱን ውሳኔና ውሳኔው በ09-02-97 ዓ.ም ለባለዕዳው የደረሰበትን ማረጋገጫ በማስረጃነት አቅርቦአል።

የፍ/ባለዕዳው በበኩሉ በ07-07-98 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፍ/ባለመብቱ ከአፈጻጸም አቤቱታው ጋር በማያያዝ ያቀረባቸውን የጽሑፍ ማስረጃዎች የአቀራረብ ሥርዓት በተመለከተ የጽሑፍ ማስረጃዎች መቅረብ ስለሚችሉበት ጊዜና ሁኔታ በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕጉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር መቃወሚያ ካቀረበ በኋላ በአማራጭ የአፈጻጸም አቤቱታውን ፍሬ ጉዳይ በተመለከተ ያቀረባቸው የክርክር ነጥቦች ባጭሩ፤

1.የባትኮዳ ደንቦች የውሎቹ የማይነጠሉ አካሎች ሆነው እንደሚቆጠሩ በዋናዎቹ እያንዳንዱ ውል በአንቀጽ 1 ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ምክንያት ደንቦቹ በውሎቹ ላይ ተፈጻሚነት ስላላቸው ደንቦቹ በውሎቹ ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው አስመስለው ባለመብቱ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑና ደንቦቹን የማሻሻል ሥልጣንም የተዋዋይ ወገኖች ሳይሆን የአውጭው ባለስልጣን (የባትኮዳ) በመሆኑ፣

2.የማሻሻያ ውሎቹ ተፈረሙ የተባሉት ኅዳር 19 ቀን 1987 ዓ.ም. ሲሆን አማካሪው መሐንዲስ በኮንስትራክሽን ተቆጣጣሪነት በባለዕዳው የተቀጠሩት ግን የማሻሻያ ውሎቹ ተፈረሙ ከተባለበት ቀን በኋላ ሁለት ዓመት የሚጠጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ በሐምሌ 25 ቀን 1989 ዓ.ም በመሆኑ ምክያት በባለዕዳው ከመቀጠራቸው ሁለት ዓመት በፊት በማሻሻያ ውሎቹ አማካሪ መሐንዲስ ሆነው ሊሰየሙ የሚችሉበት ሁኔታ ካለመኖሩም በላይ መሐንዲሱ ከባለዕዳው ጋር የነበራቸው የሥራ ውል ከጥር 4 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠና የሥራ ስንብትና ተመሳሳይ ክፍያዎች ተከፍሎአቸው ከባለዕዳው ድርጅት የተሰናበቱ በመሆኑና የሥራ ውላቸው ተቋርጦ ከባለዕዳው ድርጅት ከተሰናበቱ ከስድስት ወራት በኋላ ሐምሌ 5 ቀን 1996 ዓ.ም. በባለመብቱ ተመራላቸው የተባለውን አለመግባባት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያልነበራቸው በመሆኑ፣

3.መሐንዲሱ አቶ ወንድወሰን አበበ በመሐንዲስነት አልተሾሙም እንጂ ተሹመዋል ቢባል እንኳ ባትኮዳ ባወጣቸው መደበኛ ሁኔታዎች በአንቀጽ 2(1)ሸ በአስገዳጅነት በተደነገገው መሠረት የባትኮዳን ልዩ ፈቃድ

በጽሑፍ ሳያገኙ በደንቦቹ አንቀጽ 67 መሠረት ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ለመስጠት የማይችሉ በመሆኑና ይህንን የጽሑፍ ፈቃድ ስለማግኘታቸው ከባለመብቱ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፣

4. መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጡት በዳኝነት የተሰየመ ሰው በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ሊከተል የሚገባውን የሙግት ሥርዓት ሳይከተሉ በመሆኑ፣በተለይም ባለመብቱ አቤቱታታ ስለማቅረቡ ለባለዕዳው ሳያሳውቁ ባለዕዳውን ሳይጠሩና በባለዕዳው በኩል ሊቀርብ ይችል የነበረውን ክርክርና ማስረጃ ሳይሰሙ በመሆኑ ምክንያት ውሳኔአቸው ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ ሕጋዊ ፍርድ ሳይኖር ባለመብቱ ያቀረቡት የወጪና የወለድ ጥያቄም ተቀባይነት ሊኖረው ስለማይገባ፣

ፍ/ቤቱ በሕጋዊ መንገድ የተሰጠና ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ የለም በማለት የአፈጻጸም ጥያቄውን ሰርዞ ከተገቢ ወጪና ኪሳራ ጋር ያሰናብተን የሚል ነው::

ከመልሱ ጋር በማያያዝም በ07-07-98ዓ.ም. ከተዘጋጀ የማስረጃ መግለጫ ጋር በባለመብቱ በማስረጃነት የቀረቡትን ዋናዎቹን የግንባታ ውሎች፣መሐንዲሱ አቶ ወንድወሰን አበበ በባለዕዳው ድርጅት የተቀጠሩበትን ጊዜና የስራ ውላቸው ተቋርጦ ከስራ የተሰነናበቱበትን ጊዜ የሚያሳዩ ሰነዶችን፣ የባትኮዳ ደንቦችን አንቀጽ 2(1)ሸ እና አንቀጽ 67 ድንጋጌዎችን እና ሌሎችንም ተዛማጅ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርቧል::

የጽሑፍ ክርክሩ በዚሁ ከተጠናቀቀ በኋላ ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን አንዳንድ ነጥቦች አስመልክቶ ግራ ቀኙን በ01-09-98 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አነጋግሮ ክርክራቸውን መዝግቦአል::

አጠቃላይ ክርክሩ በዚህ የተጠናቀቀ ሲሆን ፍ/ቤቱም፤

1. ከተሻሻለው የአፈጻጸም አቤቱታ ጋር በማያያዝ ባለመብቱ ስላቀረባቸው የጽሑፍ ማስረጃዎች የአቀራረብ ሥነ ሥርዓት በባለዕዳው የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

2. መሐንዲሱ በኮንስትራክሽን ተቆጣጣሪነት በባለዕዳው በሠራተኛነት የተቀጠረው በተቆጣጣሪ መሐንዲስነት መሰየሙ ከተገለጸባቸው የማሻሻያ ውሎች ተፈረሙ ከተባለበት ቀን ሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑና ጉዳዩ በባለመብቱ የተመለከተውም መሐንዲሱ ከባለዕዳው ጋር የነበረው የሥራ ውል ከተቋረጠ ከስድስት ወራት በኋላ በመሆኑ ሥልጣን ሳይኖረው የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም መገደድ አይገባውም በማለት በባለዕዳው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

3. መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጠው ስለክርክሮች አወሳሰን አግባብነት ያላቸውን የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ሳይከተል በመሆኑ ውሳኔውን ለመፈጸም አልገደድም በማለት ከአለዕዳው የቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ነው ወይስ አይደለም?

4. መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጠው የውሉቹ አካል በሆነው በባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1) (ሸ) መሠረት የባትኮዳን ፈቃድ በጽሑፍ ሳያገኝ በመሆኑ ከስምምነታችን ውጪ በተሰጠ ውሳኔ ልንገደድ አይገባም በማለት ከባለዕዳው የቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ነጥቦች በመለየት ጉዳዩን መርምሮአል፡፧

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ባለመብቱ ከአፈጻጸም አቤቱታው ጋር የጽሑፍ ማስረጃዎች ሊያቀርብ የቻለው፣ ፍ/ቤቱ በ25-05-98 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በመሆኑ ባለዕዳው ትዕዛዙ አግባብነት ያለው አይደለም የሚል ከሆነ በይግባኝ ማሳረም የሚችል ከመሆኑ በስተቀር ጉዳዩ በዚህ ፍ/ቤት በድጋሚ ሊመረመር የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ የመቃወሚያው ክርክር በዚሁ ታልፉአል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣ባለዕዳው የማሻሻያ ውሉቹ ስለተፈረሙበት ሁኔታታ መሠረታዊ ያልሆኑና ተቀባይነት የሌላቸውን አንዳንድ የክርክር ነጥቦችን ከማቅረብ ውጪ ሶስቱንም ውሎች መፈረሙን በግልጽ አልካደም፡፡ ውሳኔውን የሰጠው አቶ ወንድወሰን አበበ መሀንዲስ ተደርጎ በባለዕዳው የተሰየመ መሆኑ ደግሞ በሶስቱም የማሻሻያ ውሎች አንቀጽ1(1) ሥር ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ወንድወሰን አበበ የኮንስትራክሽን ተቆጣጣሪ ሆኖ በባለዕዳው የተቀጠረው የማሻሻያ ውሎች ከተፈረሙ ከሁለት ዓመታት በኋላ መሆኑን ባለዕዳው ካቀረበው ማስረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ባለዕዳው የማሻሻያ ውሉቹን መፈረሙንና በውሉቹም ግለሰቡን መሀንዲስ አድርጎ መሰየሙን ያልካደ እስከሆነ ድረስ በመሐንዲሱና በባለዕዳው መካከል የሥራ ውል መቋቋሙም ሆነ መቋረጡ፣እንዲሁም የተቋቋመበትና የተቋረጠበት ቀን፣ተዋዋይ ወገኖችን ማለትም መሐንዲሱንና ባለዕዳውን ብቻ የሚመለከት ከመሆኑ በስተቀር በባለመብቱ ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት ፍ/ቤቱ አላገኘም፡፡ ጉዳዩ ለመሐንዲሱ የተመለከተ ከባለዕዳው ጋር የነበረውን የሥራ ውል ከተቋረጠ ከስድስት ወራት በኋላ ነው በማለት በባለዕዳው የቀረበው ክርክርም በተመሳሳይ ምክንያት ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ከመሆኑም በላይ የመሐንዲሱ የሥራ ውል ተቋርጦአል ከተባለ በኋላ ባለዕዳው ይህንኑ ሁኔታ ለባለመብቱ በጽሑፍ በመግለጽ ሌላ ተተኪ

መሀንዲስ የተሰየመ መሆኑን ለባለመብቱ ስለማስታወቁ ያቀረበው ክርክርና መስረጃ ባለመኖሩ በአጠቃላይ የመሐንዲሱን የቅጥርና የስንብት ቀን የማሻሻያ ውሎቹ ከተፈረሙበትና ጉዳዩ ለመሐንዲሱ ከተመራበት ቀን ጋር በማያያዝ በባለዕዳው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል።

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣በመሠረቱ መሐንዲሱ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት የአቤቱታውን መቅረብ ለሌላው ወገን ማሳወቅና በባለዕዳው በኩል ሊቀርብ የሚችለውን ክርክርና ማስረጃ መስማት የነበረበት መሆኑ ከሥነ ስርዓት ሕጉ አንጻር ተገቢ የነበረ ቢሆንም መሐንዲሱ ውሳኔ የሰጠው ይህን ስርዓት ሳይከተል መሆኑን ከውሳኔው ይዘት መረዳት የሚቻልና በባለመብቱም ያልተካደ ነው። ይሁን እንጂ መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጠው ተገቢውን የክርክር ሂደት ተከትሎ አይደለም የሚል ከሆነ ባለዕዳው ይህንኑ በማሻሻያ ውሎቹና በሥነስርዓት ሕጉ መሠረት በወቅቱ በይግባኝ ማሳረም የሚገባው ሆኖ ሳለ በዚህ መብቱ ሳይጠቀም በተገቢው ወቅት የደረሰውን የውሳኔ ግልባጭ ይዞ ከቆየ በኋላ አሁን ውሳኔውን ላለመፈጸም ይህንን ቅሬታ በመከራከሪያነት ማቅረቡ የሕግ አግባብነት ያለው ሆኖ ስላልተገኘ በዚህ ነጥብ ላይ የቀረበውንም ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም።

አራተኛውንና የመጨረሻውን ነጥብ በተመለከተ፣ባለዕዳው ያቀረበው ክርክር የባትኮዳ ደንቦች የውላችን አካል መሆናቸው በዋናዎቹ ውሎች አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተ ሲሆን መሐንዲሱ በአንቀጽ 67 መሠረት ልዩነቶችን ለመፍታት የባትኮዳን ቀጥተኛ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት የሚገባው መሆኑ በባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1) (ሸ) ሥር በአስገዳጅነት የተደነገገ በመሆኑና መሐንዲሱ ይህንን ፈቃድ ስለማግኘቱ በባለመብቱ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ባለመኖሩ፣ እንዲሁም የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1) (ሸ) በማሻሻያዎቹ ውሎች ያልተሰረዘ ወይም ያልተለወጠ በመሆኑ መሐንዲሱ የባትኮዳን ፈቃድ ሳያገኝ ልዩነቶች የሚፈቱበትን ሁኔታ በተመለከተ ከገባነው ስምምነት ውጪ የሰጠውን ውሳኔ የመፈጸም ግዴታ የለብንም የሚል ነው።

ለዚህ ክርክር ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ባነጋገረበት በ01-09-98 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ባለመብቱ ያስመዘገበው መከራከሪያ የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1) (ሸ) ከዚሁ የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 67 ድንጋጌ ጋር ተያይዞ መታየት የሚገባው በመሆኑና የደንቡን አንቀጽ 67 ድንጋጌ ደግሞ በማሻሻያ ውሎቻችን ያሻሻልነው በመሆኑ የደንቡ አንቀጽ 2(1) (ሸ) ድንጋጌ በእኛ ጉዳይ ተፈጻሚነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በማሻሻያ ውሎቻችን አንቀጽ 1(2) ሥር የባትኮዳን ደንብ አንቀጽ 1(መ) በመካከላችን ተፈጻሚ እንዳይሆን አድርገናል፤ይህም ማለት የባትኮዳን ድርጅት፣የድርጅቱን ተቋማዊ አካላትና ባለስልጣናትን፣በመካከላችን ባለው ጉዳይ የሚያገባቸው ነገር እእንዳይኖር

ተስማምተናል ማለት ነው፤መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጠው የባትኮዳን ፈቃድ ሳያገኝ ነው የሚል ከሆነ ባለዕዳው ይህንኑ ተፈጽሞአል የሚለውን ግድፈት ማሳረም የነበረበት በማሻሻያ ውሎቻችን መሰረት በይግባኝ ነው እንጂ በዚህ የአፈጻጸም ክርክር አይደለም የሚል ነው::

ከላይ ለሰፈረው የባለመበቱ ክርክር ባለዕዳው በበኩሉ፣በማሻሻያ ውሉ አንቀጽ 1(2) ሥር የተደረገው ማሻሻያ የባትኮዳን ትርጉም (ፍቺ) የሚገልጸው የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(መ) ብቻ መሰረዙን እንጂ የአንቀጽ 2(1) (ሸ) ድንጋጌን ጨምሮ የውላቸው አካል እንዲሆኑ በዋናው ውል የተስማማንባቸው የባትኮዳ ደንቦች በሙሉ መሰረዛቸውን የሚያመለክት ባለመሆኑና የባትኮዳ ደንቦች የውላችን አካል መሆኑን የሚገልጸው የዋናዎቹ ውሎች አንቀጽ 1 ድንጋጌ በማሻሻያ ውሎቹ ያልተሰረዘ ወይም ያልተሻሻለ በመሆኑ፣እእንዲሁም ባለመብቱ በማሻሻያ ውሎቻችን የባትኮዳን ደንቦች አሻሽለናል ቢልም እነዚህን ደንቦች የማሻሻል ስልጣን ደንቦቹን ያወጣው ተቋም የባትኮዳ እንጂ የተዋዋይ ወገኖች ሊሆን ስለማይችል በባለመብቱ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት በዚሁ በ01-09-98 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ክርክሩን አስመዝግቦአል::

ከላይ ከተዘረዘረው የግራ ቀኙ ክርክር አንጻር፣

1. የባትኮዳ ደንቦች የውሉ አካል መሆናቸው በዋናዎቹ ውሎች አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተ መሆኑን፣

2. የደንቦቹ አንቀጽ 2(1) (ሸ) መሐንዲሱ በአንቀጽ 67 መሰረት ልዩነቶችን ለመፍታት የባትኮዳን ቀጥተኛ ፈቃድ ማግኘት እንደሚገባው የሚደነግግ መሆኑን፣

3. ግራ ቀኙ በማሻሻያ ውሎቻቸው የባትኮዳን ደንብ አንቀጽ 67 በማሻሻል በሌላ ድንጋጌ የተኩት መሆኑን፣ስለባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1)(ሸ) ግን በማሻሻያ ውሎቹ ውስጥ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን፣

4. ግራ ቀኙ በማሻሻያ ውሎቹ አንቀጽ 1(2) ሥር አሻሽለናል የሚሉት የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(መ) የባትኮዳን ፍቺ የሚገልጽ ሆኖ «ባትኮዳ» ማለት የሕንጻና ትራንስፖርት ግንባታ ዲዛይን ባሥልጣን ሲሆን የባለስልጣኑን የሥራ ክፍሎችና ኃላፊዎችም ይጨምራል ተብሎ የሚነበብ መሆኑን፣ግራ ቀኙ ይህንን አንቀጽ ያሻሻልንበት ነው የሚሉት የማሻሻያ ውሎቹ አንቀጽ 1(2) በባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(መ) ሥር ያለው ድንጋጌ (ፍቺ) በግራ ቀኙ መካከል ባለው ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው የሚያመለክት መሆኑን፣ከዋናው የማሻሻያ ውሎቹ መረዳት ይቻላል::

መሐንዲሱ በዚህ መዝገብ እንዲፈጸም የተጠየቀውን ውሳኔ ለመስጠት በደንቦቹ አንቀጽ 2(1)(ሸ) መሰረት የባትኮዳን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ ነበረበት ወይስ አልነበረበትም የሚለውን ነጥብ ፍ/ቤቱ እንደሚከተለው መርምሮአል::

በዚህም መሠረት የባትኮዳ ደንቦች የውሎቹ አካል መሆናቸው፣በማሻሻያ ውሎቹም የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1)(ሸ) ድንጋጌ በግልጽ አለመሰረዙ ወይም አለመሻሻሉ አላከራከረም:: ይሁን እንጂ በአንቀጹ ድንጋጌ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው፣ልዩነቶችን ለመፍታት መሐንዲሱ በመሠረቱ በአንቀጽ 2(1)(ሸ) መሠረት የባትኮዳን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ የሚኖርበት ልዩነቶቹን የመፍታታት ሥርዓት የሚከናወነው በደንቦቹ አንቀጽ 67 መሰረት ከሆነ ነው:: በፍ/ቤቱ እምነት መሰረት መሐንዲሱ በአንቀጽ 67 መሰረት ልዩነቶችን የባትኮዳን ፈቃድ ማግኘት አለበት ተብሎ በአንቀጽ 2(1)(ሸ) ስር የተደነገገበት ዓይነተኛ ምክንያት መሐንዲሱ በአንቀጽ 67 መሰረት ልዩነቶቹን መርምሮ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኙ የሚቀርበው ለባትኮዳ መሆኑ በአንቀጽ 67 ስር በመደንገጉ ሲሆን ይህም መሐንዲሱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ሊቀርብለት የሚችለውን ይግባኝ የሚያየው አካል (ባትኮዳ) የጉዳዩን በመሐንዲሱ መታየት መጀመር ከወዲሁ እንዲያውቅና እንዲፈቅድ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ባለው የዘርፉ ደንብና አሠራር መሰረት ስለውሳኔ አሰጣጡ ሥርዓት ተገቢውን እገዛና ክትትል ለማድረግ እንዲያስችለው ታስቦ የተደረገ እንደሆነ ይገመታል::

በሌላ በኩል ግን ግራ ቀኙ በማሻሻያ ውሎቻቸው ባትኮዳን ደንብ አንቀጽ 67 በሌላ ድንጋጌ የተኩ ሲሆን በዚህ የአንቀጽ 67 ድንጋጌን በተካው አዲሱ ድንጋጌም መሐንዲሱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ ከባትኮዳ ውጪ በሆነ ሌላ አካል እንዲታይ በማድረግ ግራ ቀኙ ልዩነቶች የሚፈቱበትን ሥርዓት በተመለከተ በመካከላቸው ባለው ጉዳይ ባትኮዳ ምንም ዓይነት ጣልቃገብነትና ስልጣን እንዳይኖረው የተስማሙ መሆኑን ከማሻሻያ ውሎቹ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል:: በዚህም ሁኔታ የደንቦቹ አንቀጽ 2(1)(ሸ) በማሻሻያ ውሎች በቀጥታ ያልተሰረዘ መሆኑ ቢታወቅም በልዩነቶች አፈታት ሥርዓት የባትኮዳን ጣልቃ ገብነት (የመሐንዲሱን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን) የሚደነግገው የደንቡ አንቀጽ 67 ድንጋጌ በማሻሻያ ውሎቹ በሌላ ድንጋጌ መተካት ግራ ቀኙ የአንቀጽ 2(1)(ሸ) ድንጋጌ በመካከላቸው በሚኖር ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን በአንድምታ መስማማታቸውን የሚያመለክት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ያምናል:: ግራ ቀኙ በማሻሻያ ውሎቹ አንቀጽ 1(2) ሥር የባትኮዳን ፍቺ የሚገልጸው የደንቦቹ አንቀጽ 1(መ) በመካከላቸው ባለው ጉዳይ ተፈጻሚ እንዳይሆን መስማማታቸውን ልዩነቶች የሚፈቱበትን ሥርዓት በተመለከተ በመካከላቸው ባለው ጉዳይ ባትኮዳና ባለስልጣናቱ ምንም ዓይነት ስልጣን እንዳይኖራቸው የተስማሙ መሆኑን የሚያመለክት ነው ከሚባል በስተቀር ለዚህ የማሻሻያ ድንጋጌ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ፍ/ቤቱ አላገኘም:: የባትኮዳ ደንቦች የውሎቹ አካል እስከሆኑ ድረስ በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ እንደተደረጉ ውሎቹ የሚቀጠሩ በመሆኑ ምክንያት ተዋዋዮቹ እነዚህን የባትኮዳ ደንቦች በስምምነት እንደተቀበሉ ሁሉ በስምምነት ማሻሻል የማይችሉበት ምክንያት ስለሌለና ዋናዎቹ ውሎችም ሆነ የባትኮዳ ደንቦች

ይህንኑ የሚከለክሉ ስለመሆኑ ባለዕዳው ያቀረበው ክርክር ባለመኖሩ የባትኮዳ ደንቦች በአውጪው ባለስልጣን እንጂ በተዋዋይ ወገኖች ሊሻሻሉ አይችሉም በማለት ባለዕዳው ያቀረበው ክርክር በፍትሐብሔር ሕጉ ከተደነገገው የሰዎች የመዋዋል ነጻነት አንጻር ተቀባይነት ያለው አይደለም:: በዚህም ሁኔታ መሐንዲሱ ውሳኔውን ለመስጠት የባትኮዳን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ ነበረበት በማለት ከባለዕዳው የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ ፍ/ቤቱ አላገኘውም::

በመሆኑም መሐንዲሱ ውሳኔውን የሰጠው በባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1)(ሸ) መሰረት የባትኮዳን ፈቃድ ሳያገኝ በመሆኑ ከስምምነታችን ውጪ የተሰጠን ውሳኔ የመፈጸም ግዴታ የለብኝም በማለት ከባለዕዳው የቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል::

በአጠቃላይ በውሳኔው መሰረት ላለመፈጸም ባለዕዳው ያቀረባቸው የክርክር ነጥቦች ከላይ በሰፊው በተዘረዘረው ሁኔታ ተቀባይነት የላቸውም የተባለ በመሆኑ ባለዕዳው ብር 19,760,954.79 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) ለባለመብቱ እንዲከፍል መሐንዲሱ በ06-01-97 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ባለዕዳው የመፈጸም ግዴታ አለበት በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል::

የወለድ ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ በውሳኔው ላይ ስለወለድ የተመለከተ ነገር ባለመኖሩ ጥያቄው ታልፎአል:: ባለመብቱ ለአፈጻጸም ክርክሩ ያወጣውን ወጪ የመጠየቅ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝሩ ሲቀርብ የሚታይ ይሆናል::"

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የፍርድ ባለዕዳው አልመሽ ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በ25/06/2000 ዓ.ም. በመዝገብ ቁ.27478 በሰጠው ውሳኔ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል:: እንደገናም፣በዚህ ውሳኔ ላይ የፍርድ ባለዕዳው ለሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም በሰ/መ/ቁ36577 አቤቱታውን በመቀበል ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የሥር ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች ሽሮአቸዋል:: ችሎቱም በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚከተለው ፍሬ ቃል ይገኝበታል:

"<u>ዳኞች</u>:- ዓብዱልቃድር መሐመድ፣ሒሩት መለሰ፣ጸጋዬ አስማማው፣በላቸው አንሺሶ፣ሱልጣን አባተማም::

. . . . . .

ይህ ችሎትም መሐንዲሱ ሰጡ የተባለው ውሳኔ ግራ ቀኙ ካደረጉትና ከባትኮዳን አኳያ በፍርድ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም ፈቃድ የማግኘትን ቅድመ ሁኔታታ በስምምነት ያስቀሩት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የቃል ክርክራቸውን በተጨማሪ ሰምቷል፣ አቤቱታ የቀረበበትንም ውሳኔ አግባብ ካለው ሕግ አኳያ መርምሯል::

ከላይ እንደተመለከተው፣የክርክሩ መነሻ ግራ ቀኙ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አሳይታ ከተማ ውስጥ የሚሰሩትን 3 ግንባታዎች በተመለከተ ባደረጉት ውል ምክንያት የተነሳውን አለመግባባት ተመልክተው መሐንዲሱ የሰጡት ውሳኔ እንዲፈጸም የቀረበው አቤቱታ ነው:: ተጠሪ

ውሳኔው ሊፈጸም ይገባል የሚሉት ለሶስቱ ግንባታ ውሎች በተደረጉት ማሻሻያ ውሎች የዋናዎቹ ውሎች አካል የሆነው የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(ሐ)፣1(መ) እንዲሁም 67 ስለተሻሻሉና በዚህም መሰረት በሁለት ወገኖች የሚነሳውን አለመግባባት አይተው እንዲወስኑ ለአቶ ወንድወሰን አበበ ስልጣን ተሰጥቷቸው ውሳኔ ስለሰጡ፣አመልካችም ውሳኔው ደርሶት በውሳኔው ቅሬታ ካለው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይህንኑ ለተጠሪ ስላላሳወቀ ውሳኔው የመጨረሻ እና ተፈጻሚነት ያለው መሆኑ ነው በማለት ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ መሐንዲሱ በአማካሪነት አልተሾሙም፣ተሹመዋል ቢባል እንኳ የባትኮዳን ፈቃድ ስላላገኙ ውሳኔ መስጠት አይችሉም፣የባትኮዳን ደንብ ማሻሻል የሚችለው አውጪው ባለስልጣን እንጂ ተዋዋዮች ሊሆኑ አይችሉም፣የሚሉና ሌሎች ክርክሮች አቅርቦ ውሳኔው ሊፈጸም አይችልም ብሏል፡፡

ይህ ችሎትም ለአፈጻጸም ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል ነው አይደለም የሚለውን ለመመለስ በቅድሚያ ውሳኔውን ሰጡ የተባሉት መሐንዲስ ውሳኔውን ለመስጠት ስልጣን ነበራቸው ወይ የሚለውን ነጥብ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ተጠሪ፣መሐንዲሱ ውሳኔውን ለመስጠት ስልጣን ነበራቸው የሚሉት የማሻሻያ ውሎችን በመጥቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ እነዚህን ማሻሻያ ውሎች ተመለከቷል፡፡ በነዚህ ውሎች ተሻሽለዋል የተባሉት የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(ሐ)፣(መ) እና 67 ናቸው፡፡ የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 1(ሐ) መሐንዲስ ማለት የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለውና የባትኮዳ መሐንዲስ ተብሎ የተሰየመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ በማሻሻያ ውሎቹ ተሻሽሎ መሐንዲስ የሚባለው አሠሪው የሚሰይመው ወይም በየጊዜው የሚሾመው እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በግራ ቀኙ ጉዳይ አቶ ወንድወሰን አበበ መሐንዲስ ሆነው መሰየማቸውን የውሎቹ አንቀጽ 1 ያመለክታሉ፡፡

የደንቡ አንቀጽ 1(መ) ባትኮዳ ለሚለው ቃል ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን በማሻሻያ ውሎቹ ይህ የደንቡ ድንጋጌ በግራ ቀኙ ግንኙነት ተፈጻሚ እእንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

የመጨረሻው ተሻሽሏል የተባለው የደንቡ አንቀጽ 67 ሲሆን ድንጋጌው፣ ባትኮዳ የሚሰይመው መሐንዲስ አለመግባባቶችን አይቶ በሚሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለባትኮዳ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን ሲያመለክት ማሻሻያ ውሎቹ ላይ መሐንዲሱ (በአመልካች የተሰየሙት መሐንዲስ) በሚሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ያልተስማሙ ከሆነ ጉዳዩ ለሽምግልና ጉባኤ እንደሚቀርብ ያመለክታል፡፡

ከላይ በተመለከቱት የማሻሻያ ውሎች ከባትኮዳ ደንቦች የተሻሻሉት መሐንዲሱን ባትኮዳ ከሚሰይመው ይልቅ አሰሪው የሚሰይመው መሆኑን የባትኮዳ ትርጉም ለግራቀኙ ተፈጻሚ እንደማይሆን፣እንዲሁም የክርክር መፍቻ ዘዴን ሥርዓት በሚመለከት ብቻ ነው፡፡ ከነዚህ ደንቦች በቀር ሌላ ማሻሻያ ስላልተደረገ ቀሪዎቹ የባትኮዳ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1)(ሸ) በግራ ቀኙ ግንኙነት ተፈጻሚ የማይሆንበት ምክንያት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህም አለመግባባቱን መዳኘት ከመጀመራቸው በፊት በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት የባትኮዳን ልዩ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ምክንያቱም ግራ

ቀኙ ይህንን ልዩ ፈቃድ የማግኘት ቅድመ ሁኔታ ቀሪ በማድረግ ያደረጉት ግልጽ ማሻሻያ የለም። ተጠሪ፣መሐንዲሱ ይህ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋቸውም ከማለት ውጪ ፈቃድ አላቸው በማለት ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም። የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን ባትኮዳ ደንብ አንቀጽ 2(1)(ሸ)ን በተመለከተ ግራ ቀኙ ያደረጉት ግልጽ ማሻሻያ የሌለ መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን የዚህ ድንጋጌ አስፈላጊነት በአንቀጽ 67 መሰረት መሐንዲሱ የሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለባትኮዳ በመሆኑ ባትኮዳ ጉዳዩ በመሐንዲሱ መታየት መጀመሩን እንዲያውቅና እንዲፈቅድ፣እእንደአስፈላጊነቱ ስለውሳኔ አሰጣጡ ሥርዓት ተገቢውን እገዛ ክትትል ለማድረግ እንዲችል ነው፣ግራ ቀኙ ደግሞ ባትኮዳ በጉዳያቸው ጣልቃ እንዳይገባ ያደረጉ በመሆኑ ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ አለመሆኑን በአንድምታ ተስማምተዋል በማለት ነው።

የደንቡ አንቀጽ 2 መሐንዲሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሌሎች የተዘረዘሩ ጉዳዮች ለመዳኘት ከባትኮዳ ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልገው መሆኑን በአስገዳጅነት አስቀምጧል። ከድንጋጌውም መገንዘብ እንደሚቻለው መሐንዲሱ አለመግባባቶችን ከመፍታቱ በፊት ይህን ለማድረግ እእንዲችል ስልጣን የሚሰጠውን ፈቃድ ከባትኮዳ ማግኘት ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። ፈቃድ የማግኘት ግዴታ በመስፈርትነት የተቀመጠውም ፈቃድ ሰጪው አካል ጉዳዩን ለማየት የሚሰየሙት መሀንዲሶች ሥራው የሚጠይቀውን ችሎታ፣ዕውቀት ልምድ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን የሟሉ መሆን አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ብቁ ናቸው ለሚላቸው በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችላቸውን ስልጣን ለመስጠት እና እንዲሁም የግንባታዎችን ጥራት እና ደረጃ ለመጠበቅ መሆኑን ችሎቱ ያምናል። ፈቃድ የማግኘት ዓላማው ይህ ከሆነ ደግሞ ምንም እንኳን መሐንዲሱ በሰጡት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለባትኮዳ የሚቀርብ ባይሆንም መሐንዲሱ አለመግባባቶችን ለመዳኘት ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። የሥር ፍ/ቤትም ፈቃድ የማግኘት ዓላማው ጉዳዩ በመሐንዲሱ መታየት መጀመሩን ለባትኮዳ ለማሳወቅና ባትኮዳም አስፈላጊውን ክትትል እንዲያደርግ ብቻ በመሆኑ መሐንዲሱ ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋቸውም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም። በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ባትኮዳ በጉዳያቸው ጣልቃ እንዳይገባ ስላደረጉ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ተፈጻሚነት በአንድምታ አስቀርተዋል ብሏል። ነገር ግን በማሻሻያ ውሎቹ ስለ ባትኮዳ ትርጓሜ የሚናገረው አንቀጽ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ያደረጉ ሲሆን ትርጓሜውን ተፈጻሚ አለማድረጋቸው የሚያስከትለው ውጤቱ ምን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም በግራ ቀኙ ግንኙነት ባትኮዳ ምንም እንደማይመለከተው የሚያሳይ ነው ማለት ግን አይቻልም። ሀሳባቸው ይህ ቢሆን ኖሮ ይህንኑ በግልጽ ማስቀመጥ በቻሉ ነበር።

በአጠቃላይ በአሠሪው የተሰየመው መሐንዲስ በአሠሪው ከመሰየሙ በተጨማሪ አለመግባባትን ለመፍታት ስልጣን የሚሰጠውን እእና አስገዳጅ የሆነውን የባትኮዳን ልዩ ፈቃድ የማግኘት ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ይጠበቅበታል። በተያዘው ጉዳይም ምንም እንኳን በግራ ቀኙ ተዋዋይ ወገኖች የባትኮዳን ደንብ ማሻሻል ይችላሉ አይችሉም የሚለው ክርክር

እንደተጠበቀ ሆኖ ማሻሻል ይችላሉ ቢባል እንኳን ግራ ቀኙ ባደረጉት ማሻሻያ ውሎች መሐንዲሱ አለመግባባቱን አይቶ ለመወሰን ከባትኮዳ ሊያገኝ የሚገባውን ልዩ ፈቃድ የማግኘት ቅድመ ሁኔታ ያላሻሻሉ በመሆኑና መሐንዲሱም ይህን ፈቃድ ስለማግኘቱ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ስለሌለ መሐንዲሱ ውሳኔውን ለመስጠት በሕግ ስልጣን አይኖረውም። በሕግ ስልጣን የሌለው አካል የሰጠው ውሳኔ ደግሞ በ45 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሌላኛው ወገን በጽሑፍ መግለጽ ነበረበት፣ይግባኝ አልተባለበትም፣ በሚል ምክንያት ውሳኔው ሕጋዊ ውሳኔ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልበትና እንዲፈጸም የሚደረግበት የሕግ አግባብ ሊኖር አይችልም። ስለዚህም የሥር ፍርድ ቤት ከባትኮዳ ልዩ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሐንዲስ የሰጡት ውሳኔ እንዲፈጸም ትዕዛዝ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስሕተት ሆኖ አግኝተነዋል።»